


*Prolific author, diplomat and scholar Getachew Bellete shares his gripping memoir of hiding as rural shepherd. Sustained by strong faith, he detailed his struggle for survival and resistance under the cruel Ethiopian communist regime.*

**The Pen and the Shield - Amharic Edition**
By Getachew Bellete

**Order the book from the publisher Booklocker.com**
https://booklocker.com/books/14888.html?s=pdf
**or from your favorite neighborhood or online bookstore.**

# የትዝታዬ ወግ



## ሳቅ እና ሳግ

ግለ ታሪክ

ጌታቸው በለጠ

# የትዝታዬ ወግ - ሳቅ እና ሳግ

“ቸር ነውና ምህረቱም ለዘለዓለም ነውና እግዚአብሔርን አመሠግናለሁ”

**ጌታቸው በለጠ**

Copyright © 2026 Getachew Bellete

Print ISBN: 978-1-961268-03-6

Ebook ISBN: 979-8-88532-575-2

All rights reserved. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted in any form or by any means, electronic, mechanical, recording or otherwise, without the prior written permission of the author.

Published by BookLocker.com, Inc., Trenton, Georgia.

BookLocker.com, Inc.

2026

First Edition

BookLocker

Trenton, Georgia

# ማውጫ

**የንባብ ማንደርደሪያ ወግ**

ሕይወት እንዲህም እንዲያም ነች....................................................... 1

የወግ ትርክቴ አሀዱ .............................................................................7

**ምዕራፍ አንድ፤** ሳቂታዊና ፍልቅልቋ - ኮልፌ "ኮልፊቱ" ..........................................11

**ምዕራፍ ሁለት፤** ቤተሰቤ ያለፈባቸው የሃሌሉያ እና የኤሎሄ ጎዳናዎች . ...............................39

**ምዕራፍ ሦስት፤** "የተጨበጨለት ታዳጊ ጋዜጠኛ"...................................................55

**ምዕራፍ አራት፤** የፈረሰውና የተበተነው ቤተሰብ. ..................................................67

**ምዕራፍ አምስት፤** "ኩርፊያ በሸፈነው ፈገግታ" ዳግም ወደ ኮልፌ .................................73

**ምዕራፍ ስድስት፤** "ትንግርታዊው" የአብዮት ዋዜማ...............................................81

**ምዕራፍ ሰባት፤** የተገዳዳዮች አብዮት . ............................................................ 99

**ምዕራፍ ስምንት፤** የረከሰውን የቀደሰው የኢትዮጵያ የባሕል አብዮት................................ 115

**ምዕራፍ ዘጠኝ፤** ለእምነት የተከፈለ መራራ መስዋዕትነት .......................................... 123

**ምዕራፍ አሥር፤** "ከጸባኦት" ዙፋን የተላለፈ ፍርድ. ..............................................133

**ምዕራፍ አሥራ አንድ፤** "ተዓምር ያስከፈተው" የዩኒቨርስቲ ደጃፍ. ..............................137

**ምዕራፍ አሥራ ሁለት፤** ሀገርን አቅል ያሳጣው የዋዜማ ሽር ጉድ. ...............................161

**ምዕራፍ አሥራ ሦስት፤** አስጎምዥቶ የመከነ ተስፋ. ............................................165

**ምዕራፍ አሥራ አራት፤** በድርብርብ ኃላፊነት መታመን. .........................................169

**ምዕራፍ አሥራ አምስት፤** "የብዕር ሻምላ" ያማዘዘው ፍልሚያ . ..................................183

**ምዕራፍ አሥራ ስድስት፤** ብዕሬ ያዋለዳቸው መፍትሔዎች. .......................................191

**ምዕራፍ አሥራ ሰባት፤** "እግር ሲነቅሉ አስተውለው" . ..........................................197

**ምዕራፍ አሥራ ስምንት፤** ብርታትም ይዝላል፤ አቅምም ይከዳል .................................207

**ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ፤** አሜሪካ (ሚኒሶታ)- ቤቴል ዩኒቨርስቲ ..................................209

**ምዕራፍ ሃያ፤** በባዕድ ምድር ወገንን ማገልገል. ....................................................225

**ምዕራፍ ሃያ አንድ፤** የትዳሬ ደማቅ ምዕራፍ. ....................................................229

**ምዕራፍ ሃያ ሁለት፤** "ጨፍጋጋ ምዕራፍ" - በልጅ ሞት መቀጣት . ............................235

**ምዕራፍ ሃያ ሦስት፤** ወደ ደራስያን ጎራ . ........................................................239

**ምዕራፍ ሃያ አራት፤** ዝክረ ሀዲስ ዓለማየሁ . ...................................................241

**ምዕራፍ ሃያ አምስት፤** ለኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር የቀረበ የትድግና ጥሪ . ......................243

**ምዕራፍ ሃያ ስድስት፤** የደራስያን ማኅበሩ የታሪክ ተፋልሶ . ........................................245

**ምዕራፍ ሃያ ሰባት፤** ወርቃማዎቹ የአገልግሎቴ ዓመታት. ........................................249

**ምዕራፍ ሃያ ስምንት፤** ሕያው የጥበብ ጉዞዎች....................................................257

**ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ፤** ጋና - አክራ "የዲፕሎማሲ ፍልሚያዬ ድል!" ............................275

**ምዕራፍ ሠላሳ፤** ባይተዋር ያደረግን ባይተዋሩ አካዳሚ. ..........................................293

**ምዕራፍ ሠላሳ አንድ፤** የአልጀርስ ፌስቲቫል ስኬትና ፀፀት. ....................................... 301

**ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት፤** ሊቢያ - "ፊት ለፊት የተጋፈጥኩት ሤረኛ ጉባዔ". ......................... 307

**ምዕራፍ ሠላሳ ሦስት፤** ተውገርግሮ የተሻገርነው የሚሌኒዩም በዓላችን. .........................313

**ምዕራፍ ሠላሳ አራት፤** በሀዳሴ ግድባችን የአንድ ሌሊት ቆይታ. ..................................319

**ምዕራፍ ሠላሳ አምስት፤** ፐብሊክ ዲፕሎማሲያችን - "ሮጦ! ሮጦ እንዘጭ". ..................323

**ምዕራፍ ሠላሳ ስድስት፤** በሀገሬ ተሞክሮ "የከሸፈው" ረቂቅ ስውር ሤራ . ......................343

**ምዕራፍ ሠላሳ ሰባት፤** ሃሳብ አፍላቂ ምሁራን. ..................................................347

**ምዕራፍ ሠላሳ ስምንት፤** የትዝታዎቼ ማጠንጠኛ . .................................................367

የመደምደሚያ ትንፋሼ . ...........................................................................370

# ምዕራፍ ሠላሳ ሰባት
## ሃሳብ አፍላቂ ምሁራን

የዓለማችን የፖለቲካ፣ የዲፕሎማሲና የመንግሥታት አስተዳደር ዘይቤዎች ከዕለት ወደ ዕለት ተገማችና ተጠባቂ ባልሆነ ፍጥነት ሲለወጡና ሲለዋወጡ እየተመለከትን ነው። ቴክኖሎጂው ሰፊዋን ዓለም እያጠበበ በእጅ ስልካችን አማካይነት መዳፋችን ላይ ካደረሰ ዓመታት ተቆጥረዋል። ጠቃሚም ይሁኑ እንቶ ፈንቶ ብቻ መረጃዎችን ከእጅ ስልካችን ላይ ለመበርበርና ለማደን ጣቶቻችንን ከምን ጊዜውም በላይ በሚገባ አሰልጥነናቸዋል። ለመረጃ ብርበራም ይሁን መልእክት ለመለዋወጥ ቢያንስ የእጅ ስልኩን በጣቱ ሳይጠቋቁም የሚውል የሰው ዘር ይኖር ይሆን ብሎ መስጋቱ ከእውነታ አያርቅም። ዛሬ ዛሬ የእኛም ሕዝብ ጣቱንና የእጅ ስልኩን ሳያነካካ የሚውልበት አጋጣሚ የጠበበ ይመስላል። የቴክኖሎጂው ሩጫ በዚሁ ፍጥነት የሚቀጥል ከሆነ የነገይቱ የዓለማች ዜጎች ሕይወት ምን መልክ ሊኖረው እንደሚችል ለመገመት ይከብዳል። የዘመናችን ቴክኖሎጂ "በረከተ መርገም" ከሆነብን ሰነባብቷል። ዓለማችን የደረሰችበትን የተራቀቀ የዘመነ ቴክኖሎጂ ባህርይ በሀገርኛ ብሂል እናጎላምሰው ካልን "ላም እሳት ወለደች፤ እንዳትለሰው ፈጃት፤ እንዳትተወው ልጅ ሆነባት" የሚለው ገለጻ በሚገባ ዘመኑን ይገልጥ ይመስለኛል።

በእጃችን መዳፍ ላይ ጥደን በምናውለው የእጅ ስልካችንና ለልዩ ልዩ ቴክኖሎጂዎች ፈቅደን እስረኛ ለመሆን በተማረክንበት በዚህ የሉላዊነት "ዘመነ ፍዳ" በትናንት ውርስና ልማድ ብቻ "ነበርን እየተረክን" ለመኖር መሞከር እያበቃለት ይመስላል። በነባሩና ዘመን ባሸበተው አካሄድ ላይ ብቻ ተስፋ በመጣልም የሀገርን ዲፕሎማሲ በተለመደው የእርምጃ ፍጥነት እንመራለን፣ የፖለቲካ አካሄዳችንንም "በነባሩ ወግና ሥርዓት" መሠረት ያለ ለውጥ እናስቀጥላለን፣ የመንግሥትን መንበር "በለመድነው የአስተዳደር ባሕልየሙጥኝ እንዳልን አጽንተን እናቆማለን" ብሎ ማቀድና ማለም ከዘመን ጋር የመኳረፍ ያህል ጠበኛ ያደርጋል።

ሀገራትና መንግሥታት ፖለቲካቸውን፣ ዲፕሎማሲያቸውን ኢኮኖሚያቸውንና የሕዝባቸውን ዘርፈ ብዙ ማኅበራዊ መስተጋብሮች በውጤታማነት ለመምራትና ለማስተዳደር እየተቸገሩ ያሉትም ስለዚሁ ምክንያት ይመስላል። በተላመዱት ፖለቲካዊ ዶክትሪናቸው፣ ባዋቀሯቸውና በዘረጓቸው ነባር ሥርዓቶችና አሠራሮች ወይንም በአመራራቸው ዘይቤ ስኬታማ እንሆናለን ብለው ቢጨክኑም አዋጥቷቸው ትርፋማ ሊሆኑ እንደማይችሉ "ዘመነ ሉላዊነት" መልእክቱን በሚገባ ያደረሰ ይመስላል። ብዙ ሀገራትም በየደጃፋቸው እየደረሰ ያለውና እንደ አውሎ ነፋስ እየከነፈ የሚጋልበው "ሉላዊው የአዲሱ ዓለም ሥርዓት" አንገዳግዶ እንዳይጥላቸው በመስጋትና በመጠርጠር "ከእንቅልፋቸው ባንነው በመንቃት" አማራጮችን ለመመርመር ተገደዋል።

ቀድመው የባነኑ ሀገራት የፖለቲካቸው ደጋፊ ሆኑም አልሆኑ፤ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ሰላም፣ ለሀገራቸው ዲፕሎማሲና መረጋጋት፣ ዕድገትና ልማት ገለልተኛና ተቆርቋሪ የሆኑ "አራት ዐይናማ" ምሁራንን "በባትሪ" እየፈለጉ በየዕውቀታቸው ዘርፍ በማደራጀት "ለሀገራቸው፣ ለሕዝባቸውና ለሉዓላዊ ክብራቸው ዘብ እንዲቆሙ የበረኝነቱን ኃላፊነት" እስካልሰጧው ድረስ የአምስትና የዐሥር ዓመት መሪ ዕቅድ ዘርግቶ ብቻ "በአምባገነናዊ የሥልጣን ትንፋሽ" ሀገር እንምራ ማለት ትናንት ዛሬ ስላይደለ ዘመን ወለድ ፈተናውን ለመቋቋም በጭራሽ የሚሞከሩት ላይሆን ይችላል።

ምሁራኑ ራሳቸውን በነፃነት አደራጅተው ወይንም በመንግሥት ቀጥተኛ ድጋፍ እየተደጎሙ ተጽእኖ ሳይበረታባቸው በሚቀይሱትና በሚቀየስላቸው መስመር በመራመድ በሀገራቸው ጉዳይ እየፈጠኑ ስትራቴጂካዊ ጥናቶችንና ምርምሮችን በማድረግ ሕዝባቸውንና ሀገራቸውን ለማገልገል ፈቃደኛ እስካልሁኑ ድረስም መጭው ጊዜ የሚናፈቅ አይሆንም። በዚህ ጉዳይ ላይ ቀድመው የነቁ የበርካታ ሀገራት መንግሥታት ምሁራኖቻቸውን በአግባቡ ስለሚጠቀሙባቸው በብዙ ጉዳዮች አትራፊ ሆነዋል።

ለተወሰኑ ተልዕኮዎች ተሰባስበው የሚደራጁት ምሁራንን በተመለከተ የመንግሥት ሥልጣን ለያዙ ወይንም ሥልጣን ለመጨበጥ በፖለቲካ ዶግማ ተጠፍንገው ለሚፋተጉና እርስ በእርስ ለሚገዳደሩ የፖለቲካ አመለካከቶች ደጋፊ ወይንም ቃፊርና "በረኛ" መሆን ላይጠበቅባቸው ይችላል። በተቻለ መጠን ምሁራኑ ነፃና ገለልተኛ ቢሆኑ ይመረጣል። "ነፃነቱን ካልፈለጉም" መንግሥታዊ ወይንም ፖለቲካዊ ድጋፍ እየተቀበሉም ቢሆን በሙያቸው ማገልገል ይችላሉ።

ይህን መሰሉ የበጎ ፈቃደኛ ምሁራን ስብስብ ወይንም ቡድን ዓለም አቀፍ እውቅና ያገኘበት መጠሪያው "Think Tank Group" ወይንም "Policy Institute" በመባል ይታወቃል። ወደ ሀገራችን ቋንቋ ተተርጉሞ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ ስያሜ እስከ ዛሬ ይፋ ያልተደረገ ቢሆንም ለመግባባት ያህል ግን የ"Think Tank Group"ን "የዕውቀት/የሃሳብ ቋት" ወይንም "ሃሳብ አመንጪ" የምሁራን ቡድኖች ብለን ብንተረጉመው ሊያግባባን ይችል ይመስለኛል። የተሻለ ትርጉም አለኝ የሚል ካለም አመስግኜ ለመቀበል አላመነታም።

## "የቲንክ ታንክ" ታሪካዊ ዳራ

በምሁራን ስብስብ የተቋቋመ "Think Tank Group" ወይንም "Policy Institute" ("የሃሳብ ቋት") ዋነኛ ትኩረቱ በአንድ ሀገር፣ ወይንም በአንድ አህጉራዊ ቀጣና፣ ወይንም በአህጉር ደረጃና በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ በልዩ ልዩ ርዕሰ ጉዳዮች ምርምር በማድረግ ለየመንግሥታቱ የመፍትሔ ሃሳብ የሚጠቁም ወይንም የሚያመላክት ቡድን ወይንም ተቋም ነው። የምርምር ትኩረቱ በዲፕሎማሲ፣ በአድቮኬሲ፣ በፖለቲካል ስትራቴጂ፣ በኢኮኖሚ፣ በግብርናና በንግድ፣ በቴክኖሎጂ፣ በዘርፈ ብዙ ማኅበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች፣ በኪነ/ሥነ ጥበባትና በወታደራዊ መስክ ወዘተ. ላይ ጠለቅ ያለ የፖሊሲና የስትራቴጂክ ጥናት በማቅረብ ለአስፈጻሚውና ለፈጻሚው አካል ማቅረብ ነው።

እንዲህ ዓይነት ቡድኖች አገልግሎት የሚሰጡት ቁሳዊ ትርፍ ወይንም ልዩ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ አይደለም። በዋናነት የሚገዙት ለኅሊናቸውና ለሙያቸው ስለሆነ ትርፋቸው ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው የሚሰጡት የሙያ አበርክቷቸው ነው። የመንቀሳቀሻ በጀታቸው ምንጭ ራሳቸው ከሚሰሩት የማማከርና የጥናት ገቢዎች፣ ከበጎ አድራጊ ተቋማት፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ሀገር አቀፍም ይሁን ዓለም አቀፍ የተራድኦና የልማት ድርጅቶች፣ ከንግዱ ማኅበረሰብ፣ ከልዩ ልዩ ፋውንዴሽኖችና ከግለሰቦች ወዘተ. ሊሆን ይችላል። መንግሥትም ገለልተኛ ሃሳብ ሲፈልግ ለምሁራን ቡድኑ የገንዘብና የሎጅስቲክ ድጋፍ እያደረገ ጥናት ሊያስጠና ይችላል።

በእንግሊዝ ሀገር እንደተጀመረ የሚታመነው የ"Think Tank" ቡድን 200 ዓመታትን ያህል ያስቆጠረ ቢሆንም ይበልጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ አገልግሎቱ መተዋወቅ የጀመረው ግን እ.ኤ.አ ከ1945 ዓ.ም በኋላ

እንደሆነ ይታመናል[127]። የቅርብ ጊዜያት መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በአሜሪካ ብቻ በተለያዩ መስኮች የተሰማሩ ከ2500 በላይ የ"Think Tank" ቡድኖች ሲኖሩ፣ በቻይና ከ1400 በላይ እና በአህጉረ አፍሪካ ደግሞ በጠቅላላው ከ700 በላይ "የምሁራን የሃሳብ ቋት" ቡድኖች በሥራ ላይ እንደሚገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በአጠቃላይ በዓለማችን ላይ ከ8000 በላይ የ"Think Tank" ቡድኖች እንደሚገኙ ይገመታል።

የ"Think Tank" ቡድኖች ተጽእኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። "የአሜሪካ መንግሥት እየተዘወረ ያለው በ‹Think Tank›" ቡድኖች እስትንፋስና ምሪት እንደሆነ ብዙ ምሁራን ያምናሉ[128]። ይህቺንው "ታላቅ ነኝ ባይ" አሜሪካ እየተፈራረቁ ከሚመሩት ዲሞክራቶችና ሪፐብሊካን ፓርቲዎች በተሻለ ቅቡልነት የሚንቀሳቀሱት የ"Think Tank" ቡድኖች የተጽእኖ ፈጣሪነት አቅምና ብቃት እንዳላቸው ከንባቤ በተጨማሪ በዚያች ሀገር ለትምህርት በቆየሁባቸው ዓመታት በሚገባ ለመረዳት ችያለሁ።

የግብጽ "የውሃ ፖለቲካ"፣ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያቸውና የሀገራቸው የፖለቲካ ምህዋር በዋነኛነት የሚዘወረው በጡረተኛ ዲፕሎማቶችና በሀገሪቱ ውስጥና በውጭ ሀገራት በተቋቋሙ ጠንካራ የምርምር ማዕከላትና በ"Think Tank" ቡድኖች አማካይነት እንደሆነ ቀደም ባለው ክፍል ማስረጃውን አመላክቻለሁ።[129]

እነዚሁ ቡድኖች በሰጧቸው ጥናትና ምርምሮች፣ ምክረ ሃሳቦችና የስትራቴጂክ አቅጣጫዎች ተጠቅመው የበርካታ ሀገራት መንግሥታት በውስጥና በውጭ እጅግ ግዙፍ ለውጦችን አድርገዋል። የራሳቸውን ምሁራን በማድመጥም የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያቸውን ቃኝተዋል፣ የአስተዳደራቸውን ዘይቤዎች አስተካክለዋል፣ የሕዝባቸው "የከፍቶናል" ጥያቄ ተጓዳኝ ጉዳት ከማስከተሉ አስቀድሞ ችግሮችን ፈትተዋል። ከሩቅና ከቅርብ የጎረቤት ሀገራት ጋር በሚገናኙባቸው ጉዳዮች ዙሪያም ምክረ ሃሳብ በማቅረብ የጋራ ተጠቃሚነት መርህን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ረድቷቸዋል።

## ከሸፈው አከሸፉን

በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ተምረው ሕዝባቸውን በማገልገል ላይ ባሉ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ምሁራን፣ ተመራማሪዎች፣ የእምነት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና ለየትኛውም የፖለቲካ ጎራም ሆነ ቡድን ላለመወገን ቃል ገብተው ዕውቀታቸውን፣ ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን ለሀገራዊ የጋራ ዓላማ ተፈጻሚነት ብቻ

---

[127] **በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለ "Think Tank" ቡድኖች በቂ መረጃ እያደራጀ ይፋ የሚያደርገው ተቋም የሚገኘው በአሜሪካ ፔንሴልቪያ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ሲሆን "Think Tanks and Civil Socities Program - TTCSP" በመባል ይታወቃል።**

[128] **የአሜሪካ መንግስት በሚያወጣቸው ፖሊሲዎችና በዋና ዋና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ ለሀገራቸው ዘርፈ ብዙ ጥቅም በሚያስገኙ የዲፕሎማሲ፣ የኢኮኖሚ፣ የመንግሥት አስደተዳደር ጉዳዮች ወዘተ. የፖሊሲ ምክረ ሃሳብ በመስጠት ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ያሉት እንደ** The Brookings Institution (በ1961 **የተመሰረተ**), the Heritage foundation (በ1973 **የተመሰረተ**), the American Enterprise Intstitute (በ1938 **የተመሰረተ**), **ሚናቸው እጅግ የገዘፈ ነው።**

[129] Al-Ahram Center for Political and Strategic Studies (ACPSS), Egyptian Center for Economic Studies (ECES), Cario International Center for Conflict Resolution, Peacekeeping, and Peacebuilding (CCCPA).

ለማዋል የወሰኑ (የግል አቋማቸው ተከብሮላቸው) የተወሰኑ ቅን አሳቢ ዜጎች በ2000 ዓ.ም ተሰባስበው "የኢትዮጵያ የሰላም፣ የልማትና የዲሞክራሲ ሕዝባዊ የምክክር መድረክ" በሚል ስያሜ ሕጋዊውን አካሄድ የተከተለ አንድ የሃሳብ አመንጪ "Think Tank" ቡድን አቋቋሙ።

ከስያሜው ለመረዳት እንደሚቻለው መድረኩ በዋነኛነት ትኩረት ያደረገው በሰላም፣ በልማትና በዲሞክራሲ ዋና ዋና ሀገራዊ አንኳር ጉዳዮች ላይ ነበር። የውይይት መድረኩን ያቋቋሙት ምሁራን በየሙያ ዘርፋቸው ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን በእውቀታቸው፣ በጉልበታቸውና በጊዜያቸው በነፃ ለማገልገል ከፍ ያለ ፍላጎት ነበራቸው።

ከአባላቱ መካከል የአፈር ተመራማሪ ሳይንቲስቶች፣ የግብርናና የደን ባለሙያዎች፣ ኢንጂነሮች፣ የሕግ ባለሙያዎች፣ የፌዴራሊዝም ተመራማሪዎች፣ የማሕበራዊ ሳይንስ ምሁራን፣ በየቤተ እምነታቸው ከፍተኛ ኃላፊነት ያላቸው የሃይማኖት አባቶችና በማኅበረሰቡ ውስጥ አንቱታን ያተረፉ መካሪና ዘካሪ ሽማግሌዎች የተካተቱበት ስብስብ ነበር።

መድረኩ በተቋቋመ በአጭር ጊዜያት ውስጥ አባላቱ በሙሉ ለጊዜያቸው፣ ለገንዘባቸውና ለእውቀታቸው ሳይሰስቱ እጅግ አስመስጋኝ ተግባራት አከናውነዋል። የመጀመሪያ ትኩረታቸው የነበረው በወቅቱ በአዲስ አበባ ከተማ እንደወረርሽኝ ተስፋፍቶ ለተስተዋለው የመጤ ባሕልወራራ ተግዳሮት በጥናት የተደገፈ መፍትሔ ማመላከት ነበር። በዚሁ መሠረትም ከምሁራኑ መካከል ከከተማው የጸጥታ ተቋማት ጋር በመተባበር የሕዝብን ነባር ባሕልየሚያጎድፉና ወጣቶችን ወዳልተፈለገ ችግር ውስጥ የሚከቱ ተግባራት በሚከናወኑባቸው መጠጥ ቤቶችና የጭፈራ ቤቶች በቀንና በሌሊት ተመሳስሎ በመቀላቀል ቅኝትና ጥናቶች አዘጋጅተው ነሐሴ 8 ቀን 2000 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዳራሽ ውስጥ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን መንግሥታዊ የጸጥታ ክፍሎች፣ የሕዝባዊ ተቋማት መሪዎችና የሕዝብ ተወካዮችን ለውይይት በመጋበዝ የጥናታቸውን ውጤት ይፋ አደረጉ። በቀረበው ምክረ ሃሳብ መሠረትም በከተማው የጸጥታ ክፍሎች አማካይነት እጅግ አመርቂ የሆኑ አስተዳደራው እርምጃዎች ተወስደው ከሞላ ጎደል ችግሮቹ ረገብ እንዲሉ ተደርጓል።

በቀጣዩ መርሃ ግብርም "የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሀገራዊ ጠቀሜታ" በሚል ርዕስ እኔው ራሴ በመድረካችን ስም አንድ ጥናት አቅርቤ ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ከፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የተወከሉ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በተገኙበት ሰፋ ያለ ውይይት ተደርጎበታል። "ሀገራዊ ልማታችን በተፈጥሮ ሀብታችን" በሚል ርዕስም በአየር ንብረት ለውጥና በአካባቢ መራቆት ላይ የዘርፉ ምሁራን በየምርምር መስካቸው ተባድነው የደረሱበትን ውጤት ከምክረ ሃሳብ ጋር በተገቢ ሁኔታ ደረጃውን በጠበቀ ጥራዝ ተሰንዶ ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት እንዲቀርብ ተደርጓል።

ከአዲስ አበባ አቅም ግንባታ ቢሮ ጋር በመተባበርም "ሥነ ምግባር የዕድገት ሁሉ መሠረት ነው" በሚል ርዕስ "የስድስት ኪሎ ስብሰባ ማዕከል" እየተባለ በሚታወቀው አዳራሽ ውስጥ የአንድ ቀን ዐውደ ጥናት ተዘጋጅቶ የወቅቱ የትምህርት ሚኒስትር ሽፈራው ሽጉጤ፣ የትምህርት ባለሙያዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የዕድሜ ባለጸጎች፣ የተማሪ ወላጆችና ተወካዮች በተገኙበት የውይይት መነሻ ጥናት ቀርቦና ለትምህርቱ ሪፎርም የሚያግዝ ከፍተኛ ግብዓት ተሰብስቦና ተቀናጅቶ ለአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ እንዲቀርብ ተደርጓል።

በሀገራችን የደን ሃብት ላይ እየደረሰ ያለውን ቅጥ ያጣ ጭፍጨፋና ወድመት በተመለከተ በዘርፉ ከፍተኛ ምርምር ያደረጉ አባሎቻችን የተቀናጀ ጥናት በማድረግ ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም በአዲስ አበባ ማዘጋጃ

ቤት አዳራሽ "ሀገራዊ ልማታችን በተፈጥሮ ሀብታችን" በሚል ርዕስ እና በተመሳሳይም በአዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል እና በሸራተን አዲስ ለዘርፉ ተዋናዮችና የመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት ሁለት ታላላቅ የተፈጥሮ ሃብት ዓውደ ጥናቶች ተደርገዋል።

ከአማራ፣ ከቤንሻንጉልና ከኦሮሚያ ሦስቱ የዓባይ ተፋሰስ ክልሎች ጋር አብሮ ዕቅድ በመንደፍም GIZ/SLM ከተባለ የጀርመን ተራድኦ ድርጅት ጋር በመተባበር የተዘጋጀው "የዓባይ ተፋሰስ የተቀናጀ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ልማት" ጥናትም እጅግ የተደከመበት፣ ረጂም ቀናት የፈጁ የመስክ ምልከታዎች የተደረጉበት፣ ከፍተኛ ዕውቀትና ሃብት የፈሰሰበት የመድረኩ ዋና የስኬት መገለጫ ነበር ማለት ይቻላል።

ከፍተኛ የዘርፉ ተመራማሪ ምሁራንና የመድረኩ የቦርድ አባላት በተጠቀሱት የዓባይ ተፋሰስ ክልሎች ውስጥ ለረጅም ቀናት በመስክ ጥናት ላይ በመቆየት የህዳሴ ግድብን የሥራ አካሄድ ከተመለከቱ በኋላ የተፋሰሱ አካባቢዎች እንዴት ሊለሙ እንደሚገባቸው የሰሩት ጥናትና ያቀረቡት ምክረ ሃሳብ ከእያንዳንዱ የተፋሰሱ ክልል 250 በጠቅላላው ከሦስቱ ክልሎች 750 ባለሙያዎች በቀረቡት ጥናቶች ላይ ጥልቅ ውይይትና ምክክር አድርገዋል።

መድረኮቹ የተካሄዱት ሚያዝያ 2006 ዓ.ም በባህር ዳር ከተማ፣ ሰኔ 2007 ዓ.ም በአሶሳ ከተማና ህዳር 2008 ዓ.ም በአምቦ ከተማ ሲሆን ሐምሌ 2008 ዓ.ም ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ የማጠቃለያው ሥነ ሥርዓት ተከናውኗል። በዚሁ የማጠቃለያ መርሃ ግብር ላይ በሦስቱ ክልሎች የተደረጉት ጥናቶች ተጠቃለውና በምክረ ሃሳብ ተደግፈው ለአስፈጻሚው የፌዴራል መንግሥት ተሰንዶ ተሰጥቷል። በክልሎቹ ለተከናወኑት የልማት ጥረቶች ተገቢው ምሥጋና የቀረበ ሲሆን የጥናቱን ፕሮጀክት ለደገፈው መንግሥታዊ ያልሆነ የልማትና የተራድኦ ድርጅትም እንዲሁ ተገቢው ዕውቅና ተሰጥቷል። በየመድረኩ እየተገኙ ጥናቱን ከአደራ ጭምር እንዲረከቡ የተደረገው የየፌዴራልና የክልል መንግሥታት ከፍተኛ ተወካዮች ናቸው።

በ2007 ዓ.ም የተካሄደው አምስተኛው ሀገራዊ ምርጫ በሰላም እንዲጠናቀቅ ከሴንተር ፎር ዴቨሎፐመንት ስተዲስ ጋር በመተባበር ገዢውን ፓርቲ ጨምሮ ከሃምሳ በላይ የሚሆኑ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች በተገኙበት ምክክር ተድርጓል። በመስከረም 2010 ዓ.ም በኦሮሚያና በሶማሌ ድንበር አካባቢ በተፈጠረው ግጭት ዙሪያ ፕሬዚዳንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ በተገኙበት ተደጋጋሚ ውይይት ተድርጎ ጉዳዩን መልክ የሚያሲዙ የሀገር ሽማግሌዎች ተመርጠው በሁለቱ ክልሎች በመገኘት ለተፈጠረው ችግር መፍትሔ ለመስጠት ምክክር ተድርጓል።

መጋቢት 22 ቀን 2010 ዓ.ም በብሔራዊ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች በቀጥታ ሥርጭት በተካሄደው የሰላም ጉባዔ ላይ መድረካችንን በመወከል "የኢትዮጵያ ወጣቶች ለሰላም እሴት ግንባታ ሊጫወቱት የሚገባ ሁነኛ ሚናና በግጭት አፈታት ሂደት ሊኖራቸው የሚገባ ሀገራዊ ተሳትፎ" በሚል ርዕስ ረዘም ያለና ወቅታዊውን ሀገራዊ ችግሮች የዳሰሰ የጥናት ጽሑፍ አቅርቤያለሁ። ከላይ የተዘረዘሩት የመድረኩ ጥረቶች ለማሳያነት የቀረቡ እንጂ በሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች ላይም በርካታ ጥናቶች ተካሂደው ሰነዶቹ በአግባቡ ተደራጅተው ለየሚመለከታቸው ተቋማት እንዲደርሱ ተደርጓል።

# ያጨለሙብን የመድረካችን ራእይ

በ2008 ዓ.ም በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ተቀስቅሰው የነበሩት ሕዝባዊ እንቢተኝነትና ተቃውሞዎች ምን ያህል ጥፋትና ውድመት እንዳደረሱ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ወጣቶች በተለያዩ ስያሜዎች ብሔራቸውን በመወከል ራሳቸውን ከዳራጁ በኋላ የተለያዩ ሰላማዊ ሰልፎችን በማስተባበር፣ መንገድ በመዝጋትና በመንግሥት ንብረቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ ጭምር የሥርዓት ለውጥ እንዲመጣ ያልከፈሉት ዓይነት መስዋዕትነት አልነበረም። የተሻለ ሥርዓት እንዲመጣ መፈለግ ብቻም ሳይሆን ሥርዓት አልበኝነቱም ጎን ለጎን ከሕግ ቁጥጥር ውጭ ያፈተለከ እስኪመስል ድረስ ተገቢነት የጎደላቸው እጅግ አሰቃቂ ድርጊቶችም ተፈጽመው አስተውለናል።

በአጠቃላይ የሀገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶች መናጋት ጀምረው ስለነበር የዜጎች የመኖር ዋስትናም እንዲሁ አደጋ ላይ ወድቆ ግራ መጋባት የየዕለት ክስተት እስከ መሆን ተደርሶ ነበር። በዚህ ወቅት ነበር የኢትዮጵያ የሰላም፣ የልማትና የዲሞክራሲ ሕዝባዊ የምክክር መድረክን እንመራ የነበረው የቦርድ አባላት ለተከሰቱት ችግሮች መፍትሔ ሊሆኑ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ባለማሰለስ አዘውትረን እንመካከር የነበረው።

የመድረኩ የቦርድ አባላት የነበሩት ኢንጂነር ጌታሁን ሁሴን (የቦርድ ሰብሳቢ)፣ ጌታቸው በለጠ (የቦርድ ምክትል ሰብሳቢ)፣ እና አባላቱ ዶ/ር ሚናስ ኅሩይ፣ ዶ/ር አልጋነሽ ተሰማ፣ ዶ/ር መሐመድ ሽኩር፣ ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ፣ ወ/ሮ ጽዮን ተክሉ፣ አቶ ንጉሤ ዘውዴ፣ ቀሲስ በላይ መኮንን፣ አቶ በለጠ ባንቴሮ፣ ዶ/ር ዘውዱ እሸቱ፣ ሼህ ኢዘዲን ሼክ አብዱላዚዝና ሌሎች የተወሰኑ ተጋባዥ ምሁራንን፣ የሃይማኖት አባቶችንና የሀገር ሽማግሌዎችን በአማካሪነት በማካተት ተከታታይ ምክክር ከተደረገ በኋላ በአንድ ልብና ሃሳብ ከስምምነት ላይ ተደርሶ በሰላም ጉዳይ ላይ ሀገራዊ የምክክር ጉባዔ መጥራቱ አስፈላጊ መሆኑ ታመነበት።

በዚያ የጭንቅ ወቅት አንኳንስ አዘውትሮ መሰባሰብ ቀርቶ በሰላም ውሎ መግባት እንኳን አዳጋች ወደ መሆን ደረጃ ላይ ተደርሶ ስለነበር ‹‹ሀገር በመከራ ላይ መሆኗን የተረዳ ሽማግሌና የሃይማኖት አባት የለም ወይ? ምሁራን ድምጻቸው ስለምን ጠፋ? መንግሥትንም ሆነ አጥፊ ግለሰቦችንና ቡድኖችን የሚገስፁና የሚወቅሱ መካሪ አባቶችና እናቶች በሀገር የሉም ወይ? ወዘተ.›› የሚለው የሕዝብ ጩኸትና ምሬት ፋታ የሚሰጥ አልነበረም። በመሆኑም የቦርድ አባላቱ ከሀገር በላይ ምንም ነገር የለም በማለት ቤተሰቤን ሳይሉና ለነፍሳቸው ሳይሳሱ እስከ ምሽቱ አራትና አምስት ሰዓት ድረስ እየተሰባሰቡ አንድ ገዘፍ ያለ ሀገራዊ የሰላም የምክክር ጉባዔ በአስቸኳይ የሚጠራበትን ዕቅድ አጸደቁ።

ዕቅዱ ቢጸድቅም “ለጉባዔው የሚያስፈልገው የፋይናንስ ድጋፍ ከየት ሊገኝ ይችላል?” የሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት ነበረበት። የቦርድ አባላቱም ወደ ተለያዩ ከፍተኛ የመንግሥትና የግል ተቋማት ሃሳቡን በማስረዳት ድጋፍ ለማሰባሰብ የዘመቻ ያህል መንቀሳቀስ ጀመሩ። ነገር ግን ጥያቄው የቀረበላቸው መንግሥታዊ ሹመኞችና የአብዛኞቹ ተቋማት መሪዎች እንኳን ሃሳቡን ደግፎ የገንዘብ ድጋፍ ሊያደርጉ ቀርቶ “እንዴት በዚህ ክፉ ጊዜ ካላበዳችሁ በስተቀር እንዲህ ዓይነት ስብሰባ ለማድረግ ታስባላችሁ?” በማለት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ተስፋ አስቆራጭ “ምክር” በመስጠት ከጥረታችን ለማዘናጋት መሞከራቸው አልቀረም።

በመጨረሻ ደፍረን ያንኳኳነው በር በወቅቱ የፌዴራል ጉዳዮችና የአርብቶ አደሮች አካባቢ ልማት ሚኒስትርና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቦርድ ሊቀመንበር የሆኑትን የአቶ ካሣ ተክለ ብርሃንን ቢሮ ነበር። አቶ ካሣም ገለጻችንን ከልብ ካዳመጡ በኋላ አንድም በያዙት መንግሥታዊ የሥልጣን አቅም፤ ሁለትም ለወቅቱ የፖለቲካ

ሥርዓት እጅግ የቀረቡ ስለነበሩ ስብሰባው እጅግ ጥንቃቄ የሚፈልግ መሆኑን ከገለጹልን በኋላ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፋይናንስ ድጋፍና የመሰብሰቢያ አዳራሽ በመፍቀድ ሊተባበረን እንደሚችል ቃል ገቡልን።

ሚኒስትሩ አቶ ካሣ በገቡልን ቃል መሠረት ያስፈልጋል ያልነው ድጋፍ ሙሉ ለሙሉ ተገኝቶ ጉባዔው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስና ቢዝነስ ኮሌጅ በእሸቱ ጮሌ አዳራሽ ውስጥ እንዲካሄድ ዝግጅቱ ተጠናቀቀ። ስብሰባው በዋነኛነት ያተኮረው በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ተፈጥሮ የነበረው ተቃውሞና ሁከት የበርካታ ወገኖችን ሕይወት በከንቱ መቅጠፉን፣ እያስከተላቸው ያሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሥነልቦናዊ ቀወሶች እንደምን በምክክርና በፖለቲካዊ ውሳኔ ሊሰክኑ ይችላሉ የሚል ስለነበር ይህንን ሃሳብ የማይወዱ አካላት ጣልቃ በመግባት ነገሮችን ሊያዳፍኑ ሙከራ ማድረጋቸው አልቀረም። ማሳያውን ዝቅ ብዬ ለማስታወስ እሞክራለሁ።

የሆነው ሆኖ አንዴ ተገብቶበታልና ወደ ኋላ መመለስ ስለማይቻል በመንፈሳዊ አባትነት ከፍ ያለ የሕዝብ አደራ የተሸከሙ የሃይማኖት አባቶች፣ በላቀ እውቀታቸውና ምርምራቸው ትውልድንና ሀገርን በማገልገል የሚተጉ ምሁራን፣ በተመሰገነ ምግባራቸው በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያላቸው ተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች፣ የተከበሩ አባቶችና እናቶች፣ ተደማጭነት ያላቸው የሀገር ሽማግሌዎች፣ የገዳ አባቶች፣ የኪነ-ጥበባት ባለሙያዎችና የመገናኛ ብዙሃን ባልደረቦች በጠቅላላው 120 የሚሆኑ ጉባዔተኞች በጥንቃቄ ተመርጠው የታደሙበት ጉባዔ መስከረም 16 ቀን 2009 ዓ.ም ተካሄደ።

በአጋጣሚ ፕሮግራሙን የምመራው እኔ ስለነበርኩ ተወያዮች በነጻነት መወያየት እንዲችሉ የሚዲያ ባለሙያዎች የመክፈቻ ፕሮግራሙን ብቻ ቀርጸው እንዲሰናበቱ ተደርጎ የመነሻ ሃሳብ ከተሰጠ በኋላ ጉባዔተኛው አስተያየት መስጠት እንደሚችል ገና መድረኩ ለውይይት ክፍት መሆኑን ሲገልጽ ሙቶ ሃያውም ታዳሚ የተማከረ ይመስል የወቅቱን የመንግሥት አቋም በተመለከተ በልቡ ውስጥ የተዳፈነውን የብሶት፣ የብስጭትና የንዴት "እሳተ ጎሞራ" ያፈነዳው ጀመር።

ስብሰባውን መልክ አሲጌ መምራት እስከምቸገር ድረስ ነገሮች ሁሉ ከቁጥጥሬ በላይ ሆኑብኝ። በዚህ መልኩ ውይይቱን ተግባብቶ ለመምራት ስለሚያስቸግር ተሰብሳቢዎች በሦስት ቡድኖች ተከፋፍለው የየራሳቸውን ሰብሳቢና ፀሐፊ በመምረጥ ያለ ምንም ገደብ በነጻነት እንዲወያዩ ሃሳብ በመቅረቡ ይሄው አካሄድ ተግባራዊ ተደረገ።

በግሌ ከተወያዮቹ አንደበት ይወጡ የነበሩት ቃላት ተራ ንግግር ሳይሆኑ እንደ እሳት ወላፈን የሚንበለበሉ ነበሩ ማለቱ ይቀላል። ሦስቱ ቡድኖች በተሰጣቸው ጊዜ አልበቃ ብሏቸው ቢቸገሩም እንደምንም አግባብተን እያንዳንዱ ቡድን የደረሰበትን የማጠቃለያ ሃሳብ ጨምቆ እንዲያቀርብ ተወሰነ። በአፋጣኝ መፍትሔ ሊያገኙ ይገባል ብለው ያቀረቧቸው ዋና ዋና ሀገራዊ ችግሮች ተቀምረውና ተጠናቅረው ጉባዔው በጋራ እንዲተችባቸው ለውይይት ቀረቡ። ረቂቁን የማዘጋጀቱ ኃላፊነት በቡድኑ ጸሐፊዎች፣ ሰብሳቢዎችና በእኔ ላይ ወድቆ ስለነበር የገጠሙን ተግዳሮቶች ቀላል የሚባሉ አልነበሩም።

"በእኛ ቡድን አቋም የወሰድንባቸው ሃሳቦች አልተካተቱም፣ እኛ የሰጠናቸው ብዙ ሃሳቦች ተቆራርጠውብናል፣ ሁሉም ነጥቦች በበቂ ሁኔታ አልተመዘገቡም ወዘተ." የሚሉትን የየቡድኑን አስተያየቶች ለማስተናገድ ምን ያህል ግራ እንደሚያጋባና እንደሚከብድ መገመት አይከብድም። ለማንኛውም በተከታታይ ቀናትም ከተወሰኑ ጉባዔተኞች ጋር ምክክሮች ከተደረጉ በኋላ ከ2008 ዓ.ም መባቻ ጀምሮ ለተፈጠረው ሀገራዊ ቀውስ

አስተዋጽኦ አድርገዋል ተብለው በጋራ ስምምነት ላይ የተደረሰባቸው ዋና ዋና ሀገራዊ ችግሮች እንደሚከተለው በርዕስ ተከፋፍለው ተቀመሩ።

## ሀ. ከዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብት አጠባበቅ አኳያ

1. በሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ሰው በሰውነቱ እየተከበረ አይደለም፣ ያለበቂ ምክንያት ሰው ይታሰራል፤ ማን እንዳሰረ እንኳን አይታወቅም፤ ብዙዎች ከተሰቃዩና ረጅም ጊዜ ከታሰሩ በኋላ ማስረጃ አልተገኘባቸውም እየተባለ ይለቀቃሉ። ይህን ያደረገው አካልም ተጠያቂ ሲሆን አይስተዋልም። ይህ መንግሥታዊ "አሸባሪነት" ካልተገታ የሀገሪቱ ዕጣ ፈንታ የከፋ ይሆናል።

2. የሕግ የበላይነት ስለሌለ ከፍትሕ ይልቅ አንድ ባለስልጣን ወሳኝ አቅም አለው። ይህም በመሆኑ በሕግ ከማመን ይልቅ በባለስልጣናት መመካት አለያም በሕግ ተስፋ ቆርጦ መቀመጥ ባሕልእየሆነ የመጣ ይመስላል። በየትኛውም አጋጣሚ የተለየ ሃሳብ የሚያንጸባርቁ ግለሰቦች የተለያየ ታርጋ እየተለጠፈባቸውና ስም እየተሰጣቸው በተቃዋሚነት ይፈረጃሉ። ይህ አካሄድ ደግሞ መፈራራትን ከማንገሱም ባሻገር የጥላቻ እና የቂም ምክንያት ሆኗል።

3. ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት በመታፈኑ የሕዝብ ብሶት ጨምሯል። ከዚህም ጋር ተያይዞ የመንግሥት ሚዲያዎች ራሳቸው ፀረ-ሕዝብ አቋም የያዙ እስከሚመስሉ ድረስ የሕዝብን ሃሳብ በማፈንና ሕዝቡ ያልተናገረውን (ይልቁንም የካድሬዎችን ሃሳብ ብቻ በሕዝብ ስም በማቅረብ) በራሱ በመንግሥት ላይ አደጋ እየጋረጡ ይገኛሉ። ይህም አካሄድ ሕዝቡ በመንግሥት ሚዲያዎች ላይ እምነት እንዳይጥል አድርጓል። ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ አብዛኛዎቹ የግል ነፃ ሚዲያዎች በሕገ-ወጥነት ተፈርጀው በመታገዳቸው ሕዝቡ መተንፈሻ ስላጣ ብሶቱ ገንፍሎ እንዲወጣና ቁጣውን በጥፋት ድርጊቶች ሊገልጽ ግድ ሆኗል።

## ለ. የመልካም አስተዳደር ችግሮች

1. አድልኦ በከፍተኛ ደረጃ ይስተዋላል። የግል ጉዳዮችን ለማስፈጸም የእጅ መንሻ ማቅረብ ባሕልሆኗል።

2. ስልጣን ላይ ያለው አመራር ዓይኑ ተጋርዷል። ጆሮው ተደፍኗል። የባለስልጣናት ከገደብ ማለፍ በበርካታ ዘርፎች በግልፅነት ይስተዋላል። መንግሥት ሕዝብን ይንቃል። ንቀቱ ደግሞ ባሕርይው ሆኗል። የመንግሥት አሉታዊ የቋንቋ አጠቃቀም ገንቢ ከመሆን ይልቅ አፍራሽ ሆኗል። ‹‹ምንም አታመጡም›› የሚል የመንግሥት ባለስልጣን ድምጽ በድፍረትና በአደባባይ በግልፅ እየተሰማ ነው።

3. ኢህአዴግ በትግል ላይ በነበረበት ዘመን ለሕዝቡ ቃል የገባለትን መስመር ስቷል። ዲሞክራሲ ከማስፈን ይልቅ በተግባር የሚታየው አምባገነንነት ሆኗል። ይህ ደግሞ ሲቪል ሰርቪሱን ሳይቀር ሙሉ በሙሉ ወደ ፓርቲ አባልነት በመቀየሩ የመንግሥት ሠራተኛው የሕዝብ አገልጋይ መሆኑን ረስቶ የአለቅነትና የገዥነት ባህርይ ስለሚስተዋልበት ዜጎች በየሄዱበት መንግሥታዊ ተቋማት

አገልግሎት ከማግኘት ይልቅ ተንገላተውና ተዋርደው መመለሳቸው የሥርዓቱ መገለጫ እስከ መሆን ደርሷል።

4. የመንግሥት መመሪያዎች በየጊዜው ስለሚቀያየሩ ቤት ማፍረስ፣ የግብር አሰባሰብ መመሪያዎች መጣስና የመሳሰሉት ሁሉ አግባብ ባለመሆናቸው የሙስና ምንጭ ሆነዋል። ከዚህም የተነሳ ዜጎች መብታቸውን በገንዘብ ለመግዛት ተገደዋል።

5. በተለያዩ ከተሞችና አካባቢዎች በኃላፊነትና በአስተዳዳሪነት የሚመደቡ ግለሰቦች በፖለቲካ አቋማቸውና በፓርቲው ውስጥ ባላቸው ቦታ ብቻ እየተመረጡ ስለሚመደቡ የአካባቢውን ሕዝብ ጠንቅቀው አያውቁትም። በዚህ የተነሳ ከመሪነትና ከሕዝቡ ጋር ተከባብሮና ተስማምቶ ከመስራት ይልቅ የአፍራሽነት ሚና ሲጫወቱ ይስተዋላል።

## ሐ. ኢኮኖሚያዊ ችግሮች

1. ‹‹እድገት በድንገት›› የሆነበት ሁኔታ በስፋት ከመታየቱም በላይ ሌሎች የንግድ ተቋማት ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ እንቅፋቶችን ከመፍጠር ጀምሮ የሀብት ክፍፍሉ ከፍተኛ ልዩነትና ችግር እየፈጠረ ነው። የአንድ ቡድን የኢኮኖሚ የበላይነት በግልፅ ይታያል።

2. በልማትና በተለያዩ ምክንያቶች ከመሬታቸውና ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉ ዜጎች በተገቢው ልክ ካሳ ተከፍሏቸው ተጠቃሚ መሆን ሲገባቸው ይልቁንም በራሳቸው መሬትና ቦታ ላይ ለሚገነቡ ሕንጻዎችና ሌሎች የልማት ተቋማት በዘበኝነትና በጽዳት ሰራተኛነት እየተቀጠሩ ከፍተኛ የሞራልና የማህበራዊ ድቀት እየደረሰባቸው ይገኛል፤ ይህ ደግሞ ቂምና በቀልን እያስከተለ ነው።

3. ከሕዝብ ቁጥር ጋር የሚመጣጠኑ የሥራ ዕድሎችና ፖሊሲዎችን ከመፍጠር አንጻር በመንግሥት በኩል ከፍተኛ ግድ የለሽነት ይስተዋላል። ይህ ሁኔታ ደግሞ ባለፉት 25 ዓመታት ተወልደው ለወጣትነት የበቁትን ዜጎች ተስፋ ከማስቆረጡም ባሻገር ‹‹የተማሩ ቦዘኔዎች›› እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል።

4. የኑሮ ውድነት ሕዝቡን ማማረር ብቻ ሳይሆን እጅጉን አንገፍግፎታል። የተዘበራረቀው የፍጆታ ዕቃዎች ዋጋ የሕዝቡን ናላ አዙሮታል፤ መንፈሱንም አስቆጥቶታል።

## መ. ሕገ መንግስታዊ ችግሮች

1. የፌዴራል አወቃቀሩ ጎሳንና ቋንቋን መሠረት ያደረገ (Ethno-Linguistic Federalism) ለአንድነታችን ችግር ፈጥሯል። ከዚህም ባሻገር ክልሎች እርስ በርሳቸው ያላቸው መስተጋብር እንደ አንድ ሀገር በመናበብ ሳይሆን ራሳቸውን የቻሉ ሉዓላዊ ሀገር አድርገው ማሰብ ደረጃ ላይ ደርሰዋል። በዚህም ምክንያት በአንዱ ክልል ለደረሰው ችግር ሌላው ለማገዝና ለመርዳት ከመሞከር ይልቅ በምን አገባኝ መንፈስ መተያየት ሆኗል። ለአብነትም በአማራና በኦሮምያ ለተከሰቱ ችግሮች የሶማሊያ እና የአፋር ክልሎች አመራሮች የሰጡትን መግለጫ ማንሳት

ይቻላል። የክልሎች አወቃቀር የአንድ ሀገር ክፍሎች መሆናቸውን ከማረጋገጥ ይልቅ፤ በብዙ መልኩ አንዳንዱን አሳብጦ አንዳንዱን የሚያሳንስ ወደ ማድረጉ አዘንብሏል።

2. ላለፉት 25 ዓመታት የብሔር ብሔረሰቦችን በራስ የመተማመን፣ ባህልና ወግ ለማሳደግና ሀገራዊ ተሳትፎን ለማጠናከር ሲባል በመንግሥት በኩል በርካታ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም አብዛኞቹ የተሰሩት ስራዎች በብሔረሰቦች ልዩነት ላይ ብቻ ያተኮሩ እና ከዚያ በፊት በማንነታቸው ተቀባይነት እንዳልነበራቸውና እንደ ኢትዮጵያዊ እንዳልተቆጠሩ በተደጋጋሚ ሲነገራቸውና ልዩነታቸውን እንዲያሰፉ ሲደረግ በመቆየቱ የአንድነትን ስሜት ሸርሽሯል። በዚህም መሠረታዊ ምክንያት የተነሳ ኢትዮጵያዊ አንድነት በአደጋ ላይ ሊወድቅ ግድ ብሏል። ገዢው ፓርቲ በዓመታት ውስጥ በድፍረት የዘራውን ክፉ ዘር አሁን በሚገባ እያጨደ ይገኛል።

3. የድንበርንና የማንነትን ጥያቄ በኃይል ለመፍታት ሙከራ ይደረጋል። ሕገ መንግሥቱ ተጥሷል። ከፍትሕና ከስርዓቱ ውጪ ለጥቃት ያሰፈሰፈ በህቡ የተቋቋመ አካል ያለ ይመስላል።

4. በሃይማኖት ተቋማት ላይ የሚታየው የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሷል። የሃይማኖት ተቋማት ከፖለቲካ ነፃ ይሁኑ፤ ቢያንስ ፈጣሪ ጸሎታችንን እንዲሰማ ፖለቲካ ከሃይማኖት ጋር አይቀላቀል።

5. በሀገሪቱ ውስጥ በሕግ ከመመካት ይልቅ “ማን ሊረዳኝ ይችላል?” እየተባለ ወደ ፖለቲካውና ፖለቲከኞች መጠጋት የተሻለ ብልሃት ሆኗል፤ እንዲያውም ‹‹ከሕግ በላይ የሚያስብና ሕግ አይዳኘኝም›› የሚል አስተሳሰብ በዜጎች መካከል የተንሰራፋ ይመስላል።

6. ሕግ አውጪው፣ ተርጓሚውና አስፈጻሚው ነፃ አይደሉም። በተለይም በህግ ተርጓሚዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ጫና በመኖሩ ፍትህ በባለስልጣናት እጅና መልካም ፈቃድ ላይ ወድቃለች።

## ሠ. ማህበራዊ ችግሮች

1. የመከባበር ባህላችን ተሸርሽሯል፤ ከመከባበር ይልቅ መናናቅ ብሎም የአደባባይ እና በመድረክ ላይ ሳይቀር መሰዳደብ የሥርዓቱ ባሕልእየሆነ መጥቷል። መሪና ሕዝብ ተናንቀዋል።

2. ባሕልና ታሪክ ተረስተዋል። ቦታም አልተሰጣቸውም። በሀገሪቱ ውስጥ የሚተላለፉትና የሚታዩት የሚዲያ ፕሮግራሞች ወጣቱን በመልካም ሥነምግባር የሚገነቡና የሚያንፁ ሳይሆኑ ወደ አልተፈለገ የግለኝነትና የይሉኝታ ማጣት ፅንፍ እየወሰዱት ነው።

3. የሕንፃ ወይንም የመንገድ ግንባታ (Infrastructure) እንጂ የአዕምሮ ግንባታ ተዘንግቷል፣

4. የማህበራዊ ሚዲያው ችግር አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል። በተለይም ውጪ ሀገር ሆነው ማኅበራዊ ሚዲያ የሚጠቀሙትን አካላት ሕዝቡ በጥንቃቄ እንዲመለከታቸው የእኛዎቹ ሚዲያዎች ምንም ጥረት አያደርጉም። ይህ ስራ ከመንግሥት አካላት ውጪ ባሉ ታዋቂ እና

ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች አማካኝነት ቢሰራ የተሻለ ይሆናል። "ሀገሪቱን እየመራ ያለው ማኅበራዊ ሚዲያ ነው ወይንስ መንግሥት?" ወደማሰኘቱ ተደርሷል።

5. የትምህርት ሥርዓቱ ጥራት ወድቋል። የትምህርት ማስረጃ አሠጣጡና ስርቆቱ ተንሰራፍቷል። ገንዘብ የትኛውንም የብቃት ማረጋገጫ መግዛት እንደሚችል በይፋ ይስተዋላል።

## ረ. ሌሎች ችግሮች

1. ፅንፈኝነት ‹‹እኔ ብቻ አውቃለሁ›› በሚሉ ቡድኖች መካከል ብቻ ሳይሆን በራሱ በመንግሥት በኩልም በስፋት ይንጸባረቃል። አብዛኛዎቹ ፖሊሲዎች የተነደፉት ‹‹እኔ ብቻ አውቃለሁ›› በሚል መርህ ላይ በመመስረት ስለሆነ ጥያቄ ይነሳባቸዋል። ይህን ተከትሎም ከሕዝብ ጋር ለመወያየትና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለማሻሻል ፈቃደኛነት አይታይም።

2. ብዝሃነት ያለ ይመስላል እንጂ የለም። ጥቂቶች ብቻ ተጠቃሚዎች ናቸው። እያጋጠሙ ላሉት ሀገራዊ ችግሮችና ቀውሶች በመንግሥት ባለስልጣናት በኩል እንደ መፍትሔ እየተሰጠ ያለው መግለጫ አደገኛ ሁኔታን እየፈጠረ ነው።

3. በመረጃ ተደግፎ ሕዝቡን የማሳወቅ ችግሮችና ክፍተቶች ስላሉ ሕብረተሰቡ ለሙስና ለመጋለጥ ተገዷል። የፖለቲካ ምህዳሩ እጅግ በጣም ጠቧል።

4. መንግሥት የሕዝብን ጥያቄ አያዳምጥም። ሕዝቡ መንገድ የሚዘጋውና ንብረት የሚያቃጥለው በመንግሥት የመደመጥ እድሉ ስለተዘጋበት መሆኑ ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል። ለመደመጥ ዕድል ባለመሰጠቱ እንጂ የራሱን ሀብት ለማጥፋትና የራሱን ልማት ወደ ኋላ ለመመለስ ፍላጎት ኖሮት አይደለም።

5. በመንግሥት በኩል የሚስተዋሉት ዘርፈ ብዙ ችግሮች ጎላ ብለው የወጡ ቢሆንም በተፎካካሪ ፓርቲዎች በኩል ያለው ችግርም መዳሰስና እልባት ማገኘት ይኖርበታል። ተፎካካሪ ፓርቲዎች ለሀገርና ለወገን ማሰብ ይኖርባቸዋል፣ በፅሞና ቆም ብለው ማሰብና ማስተዋልም ይጠበቅባቸዋል።

6. በመንግሥት መዋቅሮችና ተቋማት ውስጥ የበሰሉና ብቃት ያላቸው ሠራተኞች አይታዩም። በበርካታ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ በጠቅላላው በአዋጅ የታዘዘ እስከሚመስል ድረስ የባለ ጉዳዮች መጉላላት፣ የጉዳዮች በአግባቡ ያለመፈፀም ያፈጠጡ ችግሮች ሆነዋል። ማንኛውም ጉዳይ ያለሙስና የማይፈፀምበት ሥርዓት ነበር ከተባለ ሊጠቀስ የሚገባው የትናንቱ ሳይሆን ይህ የዛሬው ሥርዓት መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል።

ከላይ በቀረቡት መሠረታዊ የሀገሪቱ ዝርዝር ችግሮች ላይ ተሳታፊዎቹ በጥልቀት ተወያይተው ባቀረቧቸው የመፍትሄ ሃሳቦች ዙሪያ የተለያዩ ሥጋቶችና ጥርጣሬዎች መንጸባረቃቸው አልቀረም። አንዳንድ ጉባዔተኞች "ለመሆኑ የኢህአዴግ መንግሥት የሚቀርቡለትን ሃሳቦች እውን ተቀብሎ መፍትሔ ሊሰጣቸው ይችላል?" የሚል ሃሳብ ቢያቀርቡም አብዛኞቹ ተሳታፊዎች ግን "በሕይወት የሌሉ ጓዶቻቸውና ዛሬ ላይ ያሉት የመንግሥት ባለስልጣናት ራሳቸው እስከ ሕይወት መስዋዕትነት ከፍለው ይህን መንግሥት ፈጥረዋል። ስለሆነም አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያን ከገባችበት ከዚህ ውስብስብ ቀውስ አውጥተዋት ወደፊት ለማራመድ መስዋዕትነት ከፍለውም ቢሆን ሕዝቡን ካላዳመጡና ሀገሪቱን ከገባችበት ማጥ ውስጥ እንድትወጣ ካላደረጉ በስተቀር ለእነርሱም ቢሆን አይበጃቸውም።"

የሚለው መከራከሪያ በሰፊው ተቀባይነት በማግኘቱ በዚሁ መንፈስ የተወሰኑ ሰዎች ተመርጠውና በተደጋጋሚ ጊዜያት ሰፊ የምክክር ጊዜያት ወስደው ከተወያዩ በኋላ ጨምቀው ያወጧቸው የሚከተሉት መሠረታዊ የመፍትሄ ምክረ በኢትዮጵያ ሰላም፣ የልማትና የዲሞክራሲ ሕዝባዊ ምክክር መድረክ በሚጠቀምበት የሄድ ሌተር ሸኚ ደብዳቤ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ከፍተኛ የመንግሥትና የፓርቲ የሥራ ኃላፊዎች በአስቸኳይ እንዲቀርብ ተወሰነ። ሰነዱን እንዲያቀርቡም 12 ያህል ሰዎች የልዑካን ቡድኑ አባላት ሆነው በጉባኤው ተመረጡ።

ከተመረጡት መካከል ከመድረኩ ቦርድ አመራር ውስጥ፦ ኢንጂነር ጌታሁን ሁሴን (ሰብሳቢ)፣ ጌታቸው በለጠ (ምክትል ሰብሳቢ)፣ ዶ/ር መሐመድ ሽኩር (አባል)፣ ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ (አባል)፣ ዶ/ር ሚናስ ህሩይ (አባል)፣ አቶ ንጉሤ ዘውዴ (አባል)፣ ዶ/ር አልጋነሽ ተሰማ (አባል) እና ከጉባዔተኛው መካከል፦ ዶ/ር አረጋ ይርዳው፣ ፕሮፌሰር ዳንኤል ቅጣው፣ ዶ/ር ንጉሤ ተፈራ፣ ዶ/ር ተገኝ ተካ፣ የታወቁት የሕግ ባለሙያ አቶ ሞላ ዘገየ ነበሩ።

## "ፊት የተነሳው ምክረ ሃሳብ"

1. *በሀገራችን በየትኛውም ክልል ለሚቀርቡ የሕዝብ ጥያቄዎች መንግሥት ከዋናው ባለጉዳይ ሕዝብ ጋር በመወያየት ኃይል ያልተቀላቀለበት መፍትሔ እንዲሰጥና የደም መፋሰሱና የንብረት መውደሙ በአስቸኳይ እንዲቆም። የሕይወትና የንብረት ውድመት ለደረሰባቸው ዜጎችም መንግሥት ራሱ ወይንም እንዳስፈላጊነቱ አጋር ድርጅቶችን፣ ተቋማትንና ግለሰቦችን በማስተባበር ተገቢ የጉዳት ካሣ የሚከፈልበት ሁኔታ ቢመቻች።*

2. *ደረቅ ወንጀልን ሳይመለከት በልዩ ልዩ ምክንያቶች ቀደም ብሎ በተፈጠረ ሁኔታም ሆነ ከወቅታዊው ሁኔታ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ምክንያቶች ያለፍርድ የታሰሩ ወገኖች በአስቸኳይ ከእስር ተፈተው ወደ ሰላማዊ ሕይወታቸው እንዲመለሱ ይቅርታና ምህረት ቢደረግላቸው።*

3. *በሕዝባችን መካከል በሰፋት እየተስተዋለ ያለው ሀዘንና ቅሬታ፣ ቂምና በቀል በጥልቀት ሥር ሰዶ የሀገሪቱን አንድነትና ሰላም አናግቶ ሊታረም የማይችል ጥፋት ከማድረሱ አስቀድሞ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ለሚገኙ ላኮረፉ ግለሰቦች የምህረትና የይቅርታ አዋጅ እንዲታወጅና በሰላማዊ ሁኔታ እንዲንቀሳቀሱ ቢደረግ።*

4. *የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል ለሚለው ተደጋጋሚ ጥያቄ መልስ በመስጠት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ የሚገኙ ተፎካካሪዎችም ሆኑ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች ሰላማዊ ጥሪ ተደርጎላቸው ከገዢው ፓርቲ ጋር ተቀራርበው የሚወያዩበትና የሚደራደሩበት መድረክ በአስቸኳይ ቢመቻች።*

5. *አብዛኞቹ የሀገሪቱ ወጣቶች ከአርሶ አደሩ እና ዝቅተኛ ኑሮ ካለው ቤተሰብ የወጡ በመሆናቸው ትምህርታቸውን አጠናቀው እስኪመረቁ ድረስ ምን ያህል ዋጋ እንደሚከፍሉና ቤተሰቦቻቸውም ‹‹ልጄ እየደረሰልኝ/እየደረሰችልኝ ነው›› በሚል የተስፋ ጉጉት እንደሚጠብቋቸው በግልፅ የታወቀ ነው። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ተምረው የተመረቁም ይሁኑ የተሻለ የሚሰኝ የትምህርት ዕድል ለማግኘት ያልታደሉት ወጣቶቻችን እንደ እውቀት ደረጃቸውና አቅማቸው በነፃ ተወዳድረው የሥራ ድል ያለማግኘታቸው መሠረታዊ ችግር ሆኗል። በአንፃሩም ኢፍትሐዊ በሆኑ አሠራሮች ከፍተኛ መገለሎች ስለሚስተዋሉ ወጣቶቻችን ብሶተኛ እንዲሆኑ ያስቻላቸው ይህ ሀገራዊ ችግር አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰ ስለሆነ ልዩና አጣዳፊ ትኩረት ተሰጥቶት መፍትሔ እንዲፈለግለት።*

6. ከፖለቲካ አባልነትና ወገንተኝነት ፍረጃና ማግለል በፀዳ መልኩ ትክክለኛ ባለሙያ በትክክለኛው የሙያ መስክ ተመድቦ ሀገሩን እንዲያገለግል ለማስቻል ብቃትና ችሎታን (Professionalism) ብቻ መሠረት ያደረገ የሥራና የኃላፊነት ምደባ ተግባራዊ ቢደረግ።

7. በሰላምና በመግባባት ዙሪያ ገለልተኛ ሆነው በሕዝባዊ (ፐብሊክ) ዲፕሎማሲ ሥራ የሚሰማሩ የልዑካን ቡድኖች በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገራት እየተንቀሳቀሱ የማቀራረብ ሥራዎችን መስራት እንዲችሉ በመንግሥት በኩል ሁኔታዎች ቢመቻቹ።

8. ሕዝቡን ያንገፈገፈውና ያስመረረው የመልካም አስተዳደር ብልሹነትና የተስፋፋው ሙስና አፋጣኝና ሥር ነቀል መፍትሔ እንዲሰጠው።

9. ሕዝቡ አዘውትሮ የሚያነሳቸው የፍትሕና የርትዕ ጥያቄዎች በአግባቡ ፈጣን ምላሽ እንዲያገኙ ቢደረግ።

10. የፍትሐዊ ሃብት ክፍፍል ጥያቄ በኀብረተሰቡ ዘንድ በስፋት የሚደመጥ ስለሆነ በሚሻሻልበትና በሚታረምበት ሁኔታ ላይ ልዩ ትኩረት ቢሰጥ።

11. የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን የሕዝብንና የመንግሥትን ድምፅ በግልፀኝነት ማስተናገድ እንዲችሉና አመኔታ እንዲያተርፉ በተገቢው የሙያ ዘርፍ በሰለጠኑ ምሁራንና ባለሙያዎች እየተመሩና እየተደገፉ በነፃነት ማገልገል እንዲችሉ ለውጤታማ የሚዲያ አጠቃቀም ምህዳሩ ቢመቻች።

12. የሀገሪቱ ሥርዓተ ትምህርት የሕዝባችንን አንድነትና ተከባብሮ የመኖር ዕሴቶች የሚያሰርፅ ሆኖ ቢቀረጽ።

13. የንግዱ ሥርዓት ፍትሐዊና እንደምንመኘው የነፃ ገበያ መርህን ያለአድልዎ እንዲከተል ልዩ ትኩረት ቢሰጠው።

14. ልዩነታችን ውበታችን ስለሆነ የሀገሪቱ አንድነትና የሕዝባችን ተፈቃቅሮና ተከባብሮ የመኖር እሴት እንዳይላላና አደጋ ላይ እንዳይወድቅ በጋራ መስተጋብራችን ላይ ተገቢው ሥራ ቢሠራ።

15. በቀጣይነት የሀገሪቱ ሰላምና ልማት ሳይደናቀፍ መቀጠል እንዲችል በወቅታዊ ችግሮች ዙሪያ ሕዝብና መንግሥት የሚወያዩባቸው የተለያዩ የምክክር መድረኮች ቢዘጋጁ።

16. ጠቃሚ ሃሳብ ያላቸው ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ያለተጽዕኖ ሃሳባቸውን በነፃነት ማቅረብ እንዲችሉ ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው መከበሩ ልዩ ትኩረት ቢሰጥበት።

የቀረቡት 16 ምክረ ሃሳቦች በአስቸኳይ ወደ ተግባር ተለውጠው የተቀጣጠለው የሕዝቡ ቁጣ እንዲበርድና ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ማግኘት እንዲችሉ መንግሥት በሙሉ ኃይሉ የራሱን ኃላፊነት እንዲወጣ ዘርዘር ያሉ የቃል ገለጻዎችም እንዲታከሉበት የልዑካን ቡድኑ ተስማምቷል። መስከረም 16 ቀን 2009 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስና ቢዝነስ ኮሌጅ በእሸቱ ጮሌ አዳራሽ ውስጥ ተገኝተው ስብሰባውን የተካፈሉ 120ዎቹ ጉባዔተኞች የ«ብሔራዊ መግባባት፣ የዕርቅ፣ የሰላምና የሽምግልና ምክር ቤት» አባላት በመሆን እንዲሰየሙና ከመካከላቸውም አርባ ሰዎች ተመርጠው በቦርድ መልክ እንዲያገለግሉ ጉባኤተኞች መስማማታቸው እንዲገለጽ አጽንኦት ተሰጥቶ ሰነዱ ለመንግሥት እንዲቀርብ ከስምምነት ላይ ተደረሰ። በኢትዮጵያ የሰላም፣ የልማትና የዲሞክራሲ ሕዝባዊ የምክክር መድረክ ቦርድ አስተባባሪነትም ከሚመለከታቸው የመንግሥት ከፍተኛ የሥራ መሪዎች ቀጠሮ እንዲጠየቅና ሰነዱ በልዑካን ቡድኑ አማካይነት እንዲቀርብላቸው ተወሰነ።

# የሚኒስትሩ "የመቃብር መሃላ"

ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት የፌዴራል ጉዳዮችና የአርብቶ አደሮች አካባቢ ልማት ሚኒስትር የነበሩት አቶ ካሣ ተክለ ብርሃን የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቦርድ ሊቀመንበር እንደነበሩና የውይይት መድረኩ ሊካሄድ የቻለው በእርሳቸው ፈጣን ድጋፍና ዩኒቨርስቲው ባደረገልን ትብብር ስለመሆኑ ከላይ ገልጫለሁ። ስለዚሁ ትብብራቸው ለማመስገንና እግረ መንገዱንም ለፖለቲካ ሥርዓቱ እጅግ ከሚቀርቡት ባለሥልጣናትና ካድሬዎች መካከል ተጽእኖ ፈጣሪ እንደሆኑ ይታመን ስለነበር ጉባዔተኛው ተወያይቶ የደረሰበትን ውጤት በመጀመሪያ ለእርሳቸው ማቅረቡ ስለታመነበት በደብዳቤ ቀጠሮ ተጠይቆ ተፈቀደልን። በቀጠሯችን መሠረትም ከላይ የተዘረዘሩት የልዑካኑ ቡድን አባላት በቢሯቸው ተገኘን። የጉባዔውን ጠቅላላ አካሄድ፣ ቁጣና ቁጭት የተሞላበትን የተሰብሳቢዎቹን ለሀገር የመቆርቆር ስሜትም በሚገባ አብራራንላቸው። በተቀጣጠለው ወቅታዊ ሕዝባዊ ተቃውሞ ምክንያት ሀገሪቱ በመስቀልኛ መንገድ ላይ ቆማ ግራ እንደተጋባችም ቋንቋ ሳንመርጥና በፕሮቶኮል ሳንሸበብ በሚገባ ፍርሃታችንንና ስጋታችንን አንድ በአንድ ዘርዝረን አስረዳናቸው።

ለሕዝቡ አንገብጋቢ ጥያቄዎችም መንግሥት ውሎ ሳያድር አስቸኳይ መፍትሔ እንዲሰጥ፤ የተቃዋሚዎችን ጥያቄ ተቀብሎም የሕዝቡ ቁጣ ወደ ከፋ ደረጃ እንዳያመራ በድርድርና በይቅርታ ጭምር ሀገራዊ ችግሮች በአስቸኳይ መፈታት እንዲችሉ ሳንለሳለስ አስረግጠን አሳሰብናቸው። አስጠነቀቅናቸው ማለቱ ይቀል ይመስለኛል። ከወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ከአቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ጋር ተገናኝተን ልክ ለእርሳቸው እንደገለጽነው ሁሉ የጉባዔውን መንፈስና የማጠቃለያዎቹን ዋና ዋና ነጥቦች በጽሑፍ እንድናስረክባቸውም ቀጠሮ እንዲያመቻቹልን አበክረን ጠየቅናቸው።

በውይይታችን ወቅት ያጋጠምንን ሁኔታ ከመግለጼ አስቀድሞ በግሌ ከአቶ ካሣ ጋር የነበረንን የግል እውቂያ አስታውሼ ስለ ባህርያቸው ጥቂት ልበል። ከአቶ ካሣ ተክለ ብርሃን ጋር በሚገባ የተዋወቅነው እርሳቸው በሚሰበስቡት የብሔር ብሔረሰቦች በዓል ዝግጅት ብሔራዊ ኮሚቴ ውስጥ አባል ሆኜ ለማገልገል በቻልኩባቸው ረዘም ያሉ ዓመታት ውስጥ ነበር። የብሔር ብሔረሰቦች በዓል ከመደረጉ አስቀድሞ እያንዳንዱ በዓል አዘጋጅ ክልል እያደረገ ያለውን ቅድመ ዝግጅት ለመገምገም በአብዛኞቹ ክልሎች ደጋግመን ጉዞ እናደርግ ስለነበር አቶ ካሣን በቅርበት ለማወቅ አግዞኛል።

ሰውዬው እንደ አብዛኞቹ የኢህአዴግ ባለሥልጣናት የግድ ካልከበድኩባችሁ እና ካላከበራችሁኝ የሚል ባህርይ በፍጹም አላስተዋልኩባቸውም። ሃሳባቸውን ሲገልጹም እንዳንዳንድ ዘመነ አቻዎቻቸውና የሥልጣን እኩዮቻቸው ፊታቸውን አጨፍግገውና በንግግራቸውም "ሻካራ ቃላትን" በመናገር ተናጋሪውን ለማሸማቀቅ የሚያደርጉትን ዓይነት ባህርይ አላስተዋልኩባቸውም። የሌላውን ሰው አስተያየት ሲያደምጡም ሆነ መልስ ሲሰጡ ተረጋግተው ነው። ሲላቸውም ጥሩ ተጫዋችና ቀልድ አዋቂም ጭምር ናቸው። በተለየ የፖለቲካ መነጽር ሌሎች እንደሚመለከቷቸው ሳይሆን በግሌ በሰብዓዊ ማንነታቸው የተረዳሁት ሰውን አክባሪ መሆናቸውን ነው።

ከአቶ ካሣ ጋር በተጨማሪ ያግባባንን አንድ ጉዳይ በእግረ መንገድ አስታውሼ ልለፍ። በጥቅምት ወር 2003 ዓ.ም ከኢህአዴግ ጎምቱ አመራሮች መካከል አንዱ ከሆኑት ከአቶ ህላዌ ዮሴፍ የሙያ ትብብር የሚጠይቅ አንድ ማስታወሻ ለኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር ጽ/ቤት ይደርሳል። የማስታወሻው ይዘት በአጭሩ በህዳር ወር 2003 ዓ.ም ለሚከበረው የኢ.ህዴን/ብአዴን 30ኛ ዓመት ክብረ በዓል ከኢትዮጵያ ደራስያን መካከል የተሻለ የኒስ እውቀት ያላቸው ባለሙያዎች ተመርጠው ድርጅቱ በትግል ሜዳ በነበረበት ወቅት "ታጋዮች" የጻፏቸውን የግጥም መድበል እንዲገመግሙ ትብብር እንድናደርግ የሚጠይቅ ነበር። መጽሐፏ ሚጢጥዬ የምትባል ዓይነት የግጥም መድበል ስትሆን፤ ርዕሷም፡- "73 የኢህዴን/ብአዴን የትግል መዝሙሮች" የሚል ነበር።

አቶ ህላዌ ዮሴፍ ማስታወሻው ለቢሯችን መድረሱን እንዳረጋገጡ በግል ስልኬ ደውለውልኝ "እባክህ ካላስቸገርኩህ አንድ አፍታ ቢሮዬ ብቅ ብትል?" የሚል ጥያቄ አቀረቡልኝ። እኔም ጥያቄያቸውን ተቀብዬ ይመቸኛል ባልኳቸው ቀንና ሰዓት ቢሯቸው ተገኘሁ። ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ እንዲህ በማለት ሃሳባቸውን ገለጹልኝ፤ "እናንተ ደራስያን እኛን ለመቅረብ ፍርሃት እንዳለባችሁ እናውቃለን፤ ቢሆንም ግን በፖለቲካዊ ትዕዛዝ ጫና ሳይሆን በትብብር ፈቃደኛ ከሆንክ ሌላ ሰው ከምንፈልግ ሙያህ ስለሆነ አንተ ራስህ በግጥም መጽሐፏ ላይ ኂሳዊ ግምገማ ብታቀርብ ደስ ይለናል" በማለት አክብሮት ባልተለየው ሁኔታ ጥያቄ አቀረቡልኝ።

ሳላመነታ ፈቃደኛነቴን ከገለጽኩላቸው በኋላ የምትገመገመውን ሚጢጢዬ መጽሐፍና ተጨማሪ "ሶረኔ" የምትል ሁለተኛ የግጥም መጽሐፍ እንዳነብ ሰጥተውኝ ተሰነባበትን። እኔ ብቻ ሳልሆን የቀድሞ የአዲስ አበባ ከተማ አፈጉባዔ የነበረችውና በኋላም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሥነ ጽሑፍና የፎክሎር መምህርቷ ጓደኛችን ስንቅነሽ አጣለ (ዶ/ር)፣ ጌታሁን አማረ (ዶ/ር)፣ አቶ ደረጀ ገብሬ፣ አቶ ታደለ ገድሌ፣ አቶ አበረ አዳሙ እና ሌሎች ጓደኞቻችንም ከሥራ አስፈጻሚ አባላቶቻችንና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተውጣጥተን ህዳር 10/2003 ዓ.ም. በባህርዳር ከተማ በተከበረው የድርጅቱ 30ኛ ዓመት ክብረ በዓል ላይ ተገኘን። የጥናት ወረቀት ያዘጋጀነውም በተመደበልን ሰዓት አቀረብን።

ለእኔ የደረሰችኝ 73 ግጥሞችን የያዘችው መድበል የተጻፈችው ከ1975 - 1981 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት በትግል ሜዳ በነበሩበት ጊዜ በ12 ያህል ገጣሚያን ነበር። ለጥናቴ እንዲመቸኝ ከአሥራ ሁለቱ ገጣሚያን መካከል ለማሳያነት የመረጥኩት የሦስቱን ማለትም የህላዌ ዮሴፍን 24፣ የመዝሙር ፈንቴን 25፣ የታደሰ ካሣን 8 በድምሩ 57 ግጥሞች ብቻ ነበር።

በኢህአዴግ ዋና ዋና ሹመኞችና ካድሬዎች ጢም ብሎ በሞላው አዳራሽ ውስጥ የጥናት ጽሑፉን ሳቀርብ ምንም እንኳን ያልለመድኩት ዓይነት ዐውድ ቢሆንም እጅግም ድባቡ የሚከብድ አልነበረም። ሰፋ ያለ ጥናቴን ያጠቃለልኩት በሚከተለው ምጥን ድምዳሜ ነበር።

"የህላዌ ግጥሞች የምናብ ምጥቀት አድማሱ ሩቅ ነው፣ ነገውን በፍፁም አጨፍግጎ አይመለከትም። አይረሴ ምስል ከሳች ዘይቤዎችን በምልዓት በመጠቀምም መልዕክቶቹ እንዲደመጡና ለሁልግዜም እንዲታወሱ ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጓል። ለአብነትም "እንዳያልፉት የለም" የሚለው የታጋዮቹ ገናና የመዝሙር ግጥሙን መጥቀስ ይቻላል። በአንፃሩ የመዝሙር ፈንቴ ግጥሞች በአብዛኛው የተዋቀሩት ሕዝባዊ ሥነ-ቃልን እንደ ዋነኛ ግብዓት በመጠቀም ነው። በርካታ ሕዝባዊ ግጥሞችን፣ ዘይቤዎችንና የሕዝቡን የዕለት ተዕለት ቋንቋ በመጠቀም ከሕዝብ ልብ ለመድረስ ጥረት አድርጓል። የታደሰ ካሣ ግጥሞች ትግሉንና የትግሉን አባላት እንደ ቤተሰብ የሚያስተሳስሩና በቤተሰባዊ እሴቶች ዙሪያ ያተኮሩ ናቸው" የሚል ሆኖ ይዘቶቹን በይበልጥ ግልጽ አድርጌ ለማስረዳት የሚያስችሉኝን ክብ ሥዕሎች ለማሳያነት ለመጠቀም ሞክሬያለሁ።

የህላዌን ዋና ጭብጥ "ዓለም አቀፋዊ" ይዘት ስለነበረው ሰፋ ባለ የክብ ቅርጽ፣ የመዝሙር ፈንቴን ደግሞ በተወሰነ የሕዝብ ክፍል ላይ ስላተኮረ በመለስተኛ ክብ እና ታደሰ ካሣ በዋነኛነት በቤተሰብ ላይ ስላተኮረ አነስ ባለ ክብ ነበር የወከልኩት። አቅርቦቱ ተጠናቆ ለሻይ እረፍት እንደወጣን በአቶ ካሣ አሰባሳቢነት በርከት ያሉ አብሮ አደግ "የትግል ጓደኛማቾቹ" ተጠራርተው እኔን በመሃላቸው አቁመውኝ በጥናቴ የደረስኩበትን ድምዳሜ እየጠቃቀሱ ለዛ ባለው ጓዳዊ ቤተሰብነት እርስ በእርስ መተራረብ ጀመሩ።

"ህላዌ ዱሮም አመለካከትህ ሩቅ ነበር። ታዴ የቤተሰብ ነገር ስለማይሆንለት በትግል ላይ እያለንም ቤተሰቦቻችን እንዴት ሆነው ይሆን? እያልክ ትተክዝ ነበር። መዝሙር ፈንቴ ያው "ሕዝባችን" ማለትን ዱሮም ስለተካነበት የጻፈው የሚናገረውን ነው ወዘተ." እየተባባሉ እርስ በእርስ መበሻሸቃቸውን አስታውሳለሁ። አቶ ካሣ ተክለ ብርሃን ከዚያን ዕለት በኋላ በተገናኘንበት አጋጣሚ ሁሉ ያንን የግጥም ግምገማ እያስታወሱ "ሦስቱንም የገለጽካቸው በትክክል ነበር" በማለት ጓዶቻቸው እርስ በእርስ የተተራረቡባቸውን ቀልዶች እያነሱ እንሳሳቅ ነበር።

ቢሯቸው በተገኘንበት ዕለት ግን በአቶ ካሣ ላይ ያስተዋልኩት ባህርያቸው ያ ቀደም ሲል የማውቀውን ዓይነት ግልጽና ተጫዋች ባህርያቸውን ሳይሆን በፍጹም የተለየ ሆነውብኝ ነበር። የመሰላቸት ዓይነት ስሜትም አስተውዬባቸዋለሁ። ከቃል ገለጻችን በማስከተል ተጠንቅቀን የቀሸርናቸውን አሥራ ስድስቱን ነጥቦች የልዑካን ቡድኑን በመወከል ማንበብ ስጀምር ፊታቸውን በማኮሳተር ቀድሞ ከለመድኩት ባህርያቸው በተቃረነ ሁኔታ የንዴት ስሜት እየተስተዋለባቸው እንደሚያደምጡኝ ሳስተውል ግራ መጋባቴ አልቀረም። አላውቃቸውም ነበር ወይንስ ምን የሚያስከፋ ሃሳብ ሰነዘርኩ እያልኩ የተቆጣ ስሜታቸውን በስሜቴ እያነበብኩ በወረቀት ላይ የሰፈሩትን ነጥቦች አንድ በአንድ አንብቤ እንደጨረስኩ ሰነዱን እንድናስረክባቸው ፋታ እንኳን ሳይሰጡን፦

"ለመሆኑ ደጋግማችሁ እርቅ፣ ብሔራዊ መግባባት፣ ይቅርታ" እያላችሁ አቋም ያያዛችሁት ማንን ከማን ለማስታረቅና ለማግባባት አስባችሁ ነው። እናንተ ያቀረባችሁት እርቅና ብሔራዊ መግባባት ተግባራዊ ይሁን እንኳን ቢባል ሊተገበር የሚችለው በኢህአዴግ መቃብር ላይ ብቻ ነው። ማን ከማን ተጣልቶ ነው ብሔራዊ እርቅ የሚያስፈልገው? በሀገሪቱ ውስጥ ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር እየሠሩ ያሉት እነማን እንደሆኑ በሚገባ እናውቃለን። ይልቅስ የየብሔራቸውን ስያሜ በመያዝ በየአካባቢው አመጽ እየቀሰቀሱና እያስተባበሩ ያሉትን የወጣት ስብስብ ቡድኖችና እነርሱን መጋለቢያ እያደረጉ መረጋጋት የነሱንን ግለሰቦችና ቡድኖች አደብ እንዲገዙና ወደ ቀልባቸው እንዲመለሱ ምከሯቸው። በምሁርነት ስም ነገር የሚያወሳስቡትን ጓደኞቻችሁንም አስታግሷቸው። ኢህአዴግ ከማንም ጋር አልተጣላም፤ ከማንም ጋር ለድርድር አይቀመጥም…።" ሌላም መሰል ሃሳቦችን ባልተረጋጋ ስሜት ውስጥ ሆነው እየተወራጩ ሃሳባቸውን ደመደሙ።

ንግግራቸውን እንደቋጩ ሁላችንም በመልሳቸው ደንግጠን አንገታችንን በመድፋት ለደቂቆች ያህል ቢሯቸው ዝምታ አርብቦበት ጸጥ እረጭ አለ። ዝምታውን ለመስበር አስበው ነው መሰለኝ እንደገና ጭንቅላታቸውን እየወዘወዙ፦ "እኔ ብቻ ሳልሆን የተቀሩት ጓዶቼ ጭምር የተቀመጥንባቸው የሥልጣን ወንበሮቻችን እንደ እሳት እንደሚፋጁ የተረዳችሁ አይመስለኝም። በግሌ ኃላፊነቴን እየተወጣሁ ያለሁት በጀርባ ህመም እየተሰቃየሁ ጭምር ነው። ሰሞኑን ራሱ የከረምኩት ሕክምና ላይ ነው። ተመችቶኝ እንዳይመስላችሁ። የተቀመጥኩበት ወንበር የሚፋጅ ፍም ነው…" ዝምታችን ይበልጥ ከብዶ ከመካከላችን ማን ቀድሞ እንደሚናገር እርስ በእርስ መተያየት ጀመርን።

ድንገት የአዲስ አበባው የሥነ ትምህርት ምሁሩ ዶ/ር ተገኝ ተካ የውስጣቸውን ቁጣ በገጽታቸው እያስነበቡ፦ "አቶ ካሣ ይህቺ ሀገር የሁላችንም ናት። ሌላ ተለዋጭ ሀገር የለንም፤ ሊኖረንም አይችልም። እያንዳንዳችን በሀገራችን ጉዳይ ያገባናል በማለት በነፃነት ተወያይተን ምክረ ሃሳባችንን ለመንግሥት ለማቅረብ የወሰንነው ችግሮቹ ሳይባባሱና ሀገሪቱም የከፋ አደጋ ላይ ከመውደቋ አስቀድሞ መፍትሔ እንዲሰጥበት እንጂ ምንም የተለየ ዓላማ ኖሮን አይደለም። ከኮሌጅ ተማሪነታችን ጀምሮ ስንታገል፣ ስንታሰርና ስንሰደድ የኖርነው በዚህች ሀገር ዲሞክራሲ ሰፍኖ የሕዝቦች እኩልነት ተከብሮ ለመኖር እንጂ የተለየ ፍላጎት ኖሮን አይደለም። ያ ከተማሪነታችን ዘመን ጀምሮ የከፈልነው መስዋዕትነት እንደዚህ ከንቱ ሆኖ መመልከት እጅግ ያሳዝናል…" ንግግራቸውን ሳይጨርሱ እልህ እየተናነቃቸው እየተንቀጠቀጡ እንባቸውን ያፈሱ ጀመር። ሁላችንም ያደመጥናቸው በድንጋጤ ስሜት ውስጥ ተዘፍቀን ነበር።

ከዶ/ር ተገኝ ቀጥሎ ፕሮፌሰር ዳንኤል ቅጣውም እጅግ እንዳዘነ ጠንከር ባሉ ቃላት ስሜቱን በመግለጽ "መንግሥት ይህንን የተቀጣጠለ ችግር በንግግርና በውይይት መፍታት እስካልቻለ ድረስ ውጤቱ የከፋ ሊሆን እንደሚችል አልጠራጠርም።" በማለት ሃሳቡን ደመደመ። ከዚያ በኋላ ማንም ምንም ሃሳብ ለማቅረብ ፈቃደኛ ስላልነበረ የተወሰኑ ደቂቆች በዝምታ ካለፉ በኋላ ፈቃደኛ ሆኑም አልሆኑ ተስፋ ሳንቆርጥ ይህንንው ምክረ ሃሳብ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዘንድ ማድረስ እንድንችል የእርሳቸውን ትብብር ጠየቅን። ብዙም አላመኑቱም፦ "መልካም ጠቅላይ ሚኒስትሩም የተለየ አቋም ይኖራቸዋል ብዬ አልገምትም። ለማንኛውም ግን ማነጋገር የምትፈልጉ ከሆነ ቀጠሮ እንዲይዙላችሁ ልነግርላችሁ እችላለሁ። እናንተም ማስታወሻ ላኩላቸው።" በማለት ይዘን የሄድነውን ሰነድ ለበጣ በታከለበት ሁኔታ ከእጃችን የመንጠቅ ያህል ተቀብለው ስብሰባውን ዘግተው አሰናበቱን።

የልዑካን ቡድኑ አባላት ወደየመኪኖቻቸው የገቡት እጅግ አዝናው እየቆዘሙ ነበር። የተወሰንን የቦርድ አባላት ወደ ኋላ ቀረት ብለን እርስ በእርስ ከተጽናናን በኋላ ኢንጂነር ጌታሁን ሁሴንና እኔ የቀጠሮ ደብዳቤ አርቅቀን ለጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ እንድናስገባ የቤት ሥራ ተሰጥቶን እንዳዘንንና እንደጨፈገገን ተለያየን።

## ጠቅላይ ሚኒስትሩም "የመቃብር መሃላውን" አጸኑት

ለጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ቢሮ ደብዳቤው ባስገባን በአጭር ቀናት ውስጥ ጥያቄያችን ተቀባይነት አግኝቶ የቀጠሮ ቀንና ሰዓት ተወስኖ እንድንገኝ ተገለጸልን። ቀደም ብለው አቶ ካሣን ካነጋገሩት የልዑካን ቡድን አባላት መካከል ኢንጂር ጌታሁን ሁሴን ተስፋ ሳይቆርጥ አንድ አሥር ያህሉን የመማጠን ያህል አግባብቶ እሺ ስላሰኛቸው በቀጠሯችን መሠረት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር በሚኖረው ስብሳባ ላይ ለመገኘት ፈቃዳቸውን ገለጹልን። ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ጋር ቀደም ባሉት ኃላፊነቶቻቸው ላይ ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ስለ "የኢትዮጵያ የሰላም፣የልማትና የዲሞክራሲ ሕዝባዊ የምክክር መድረክ (ኢሰልዲ)" እንቅስቃሴ ለማስረዳት ተደጋጋሚ እድል አግኝተን ስለነበር ስናገኛቸው ለሄድንበት ዋና ጉዳይ እንግዳ ይሆናሉ ብለን አልገመትንም።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተቀበሉን በፈገግታ በታጀበ ታላቅ አክብሮት ነበር። ትህትናና ሰው አክባሪነት በግልጽ ይስተዋልባቸዋል። በግሌ ደጋግሜ እንደገለጽኩት አንድን ግለሰብ በፖለቲካ እምነቱ ወይንም በሚያራምደው ርዕዮተ ዓለም መነጽር እየተመለከቱ ከሰብዓዊ ባህርይው ጋር በመሸረብ መበየን አግባብ ነው ብዬ አላምንም። ሰውን በሰውነቱ መቀበል፣ የፖለቲካ አቋሙንም በቦታውና በዐውዱ እየፈተሹ አስተያየት መስጠቱና መተቸቱ የሚሻል ይመስለኛል። በዚሁ አመለካከቴ መስፈርትነትም ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያምን ባገኘኋቸው የተወሰኑ አጋጣሚዎች ሁሉ ስለ እርሳቸው የተረዳሁት ነገር በግል ሰብእናቸው ግልጽ፣ ትሁትና አቋማቸውን በድፍረት ለመግለጽ የማያመነቱ መሆናቸውን ነው። ቢሯቸው የተገኘነውን የልዑካን ቡድን አባላትም የተቀበሉን በዚሁ በገለጽኩት ባህርያቸው ተገቢውን አክብሮት በመስጠት ነበር።

ለተወሰኑ ደቂቃዎች ያህል የአንዳንዶቻችንን ስም እየጠሩ ከሄድንበት ጉዳይ ውጭ አንዳንድ የየግል አገልግሎታችንንና የሥራ መስካችንን በመጠቃቀስ "እየበረታችሁ ነው" በማለት ከባዱን የቢሯቸውን የፕሮቶኮል ጥላ ቀለል አደረጉልን። በተለይም ዶ/ር አረጋ ይርዳው "መቼም ጊዜ እንደሌለዎት ይገባኛል፤ ቢሆንም በሚኖርዎት ትንሽ እረፍት ጊዜ ይህቺን መጽሐፌን ያንብቡልኝ" በማለት መጽሐፋቸውን አበረከቱላቸው። "ስንፍና ካልሆነ በስተቀር ለንባብ ጊዜ አይጠፋም" በማለት ስለ ስጦታው ካመሰገኗቸው በኋላ "እሺ ምን እንታዘዝ?" በማለት የሄድንበትን ጉዳይ እንድናስረዳ በር ከፈቱልን። ሰብሳቢያችን ኢንጂነር ጌታሁን ሁሴን ስለ መድረካችንና ስለ ተገኘንበት ዋና ጉዳይ አጭር ገለጻ ካቀረበ በኋላ በጽሑፍ አዘጋጅተን ይዘን የሄድነውን ነጥቦች እንደፈረደብኝ በንባብ እንዳቀርብ እኔን ጋበዘኝ። መለስተኛ የቃላት ማሻሻያ ካልሆነ በስተቀር በንባብ ያቀረብኩት ጽሑፍ በአቶ ካሣ ቢሮ ካቀረብነው ጋር ሙሉ ለሙሉ ይዘቱ ተመሳሳይ ነበር።

ነጥቦቹን በንባብ አቅርቤ እንደጨረስኩ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም በምክረ ሃሳብ ደረጃ የዘረዘርናቸው ነጥቦች መልካም እንደሆኑ ከገለጹልን በኋላ በወቅታዊው ሀገራዊ ጉዳዮችና በልማቱ ዘርፍ እየተተገበሩ ያሉትን የመንግሥታቸውንና የፖለቲካ ፓርቲያቸውን የኢህአዴግን ጥረት በዝርዝር ከገለጹልን በኋላ ድንገት ወንበራቸውን ወደ ጎን በማሽከርከር ፊታቸውን ከእኛ አዙረው ልክ እንደ አቶ ካሣ ተክለ ብርሃን ሁሉ፦ "አንዳንዶቹን መልካም ነጥቦች እኛም እየመከርንባቸው ነው። መንግሥት ብሔራዊ እርቅና ይቅርታ ያድርግ ያላችሁት ሃሳብ ግን በመሠረቱ ተገቢም አግባብም አይደለም። እርቅ የሚያስፈልገው ማን ከማን ጋር ስለተጣላ ነው? ማነው ይቅርታ ሰጭ? ማንስ ነው ይቅርታ የሚቀበለው? እንደ መንግሥት ከማንም ጋር ጠብም ሆነ ግጭት የለንም። የሀገሪቱን ሰላም እያወኩ ያሉት በብሔራቸው ስም የተሸፈኑ ጥቂት ቡድኖች ናቸው።"

"እነርሱም ላይ ቢሆን በአግባቡ መንግሥት አስተማሪ እርምጃ እየወሰደ ነው። ይልቅስ እስከ ዛሬ ድረስ ሆድና ጀርባ በመሆን ጠባቸው ያልበረደውንና ባረጀና ባፈጀ አስተሳሰብ እርስ በእርስ የሚቃረኑትን የስልጣዎቹን ጓደኞቻችሁን አስታርቋቸው። ችግሩ ያለው እነርሱ ዘንድ ነው። ኢህአዴግ ከማንም ጋር አልተጋጨም፣ አልተጣላም፣ ይቅርታም አይጠይቅም። እርቅና ብሔራዊ መግባባት የምትሉት ሃሳብ ገዢውን ፓርቲያችንን የሚመለከት ስላይደለ የተጣሉ ካሉ እነርሱን አስታርቋቸው። የሀገርን ሰላም እየበጠበጡ ካሉ ቡድኖች ጋር እርቅና ድርድር መደረግ ካስፈለገ ግን ተግባራዊ የሚደረገው በኢህአዴግ መቃብር ላይ ብቻ ነው።"

ከአቶ ካሣ ቀጥሎ ሁለተኛ ዙር ድንጋጤ። "በኢህአዴግ መቃብር ላይ ብቻ" የሚሏት ሀረግ ለካንስ የገዢው ፓርቲ አባላት በአንድ የዜማ ቅኝት የሚዘምሩላት ዋናና የማትናወጥ መመኪቻ ጋሻቸው ኖራለች። በሁላችንም ስሜት ላይ በረዶ የተደፋ ያህል የውስጥ ቅዝቃዜ እየተሰማን ጠቅላይ ሚኒስትሩን ተሰናብተን ወጣን። ልክ ከቢሯቸው ወጥተን ትንሽ እንኳን ሳንርቅ ዶ/ር አረጋ ይርዳውና በርከት ያሉ የልዑካን ቡድኑ አባላት በአንድ ድምጽ "ድጋሚ ልታስድቡን ነው ያመጣችሁን? ይህ ጉዳይ ይቅርብን አትጥሩን እያልናችሁ ለምን እዚህ ችግር ውስጥ ትጥሉናላችሁ..." በማለት ቅይማታቸውንና ሀዘናቸውን በተጎዳ ስሜት ይገልጹልን ጀመር። እኛ የቦርድ አባላት ተብዬዎች ልናግባባቸው ብንሞክርም ቀሪዎቹ የልዑካን ቡድን አበላት ሊረጋጉ ስላልቻሉ በንዴት እንደጦፉ እዚያው በቆምንበት ጥለውን እብስ አሉ። እውነታቸውን ነበር። ከዚህም በላይ ቢናገሩ ይገባቸዋል።

ከሀገሪቱ ጫፍ እስከ ጫፍ ተቃውሞና የሕዝብ አመጽ ተቀጣጥሎ በንጹሐን ዜጎች ሕይወትና በሀገሪቱ ሀብት ላይ ያን የመሰለ ጥፋትና ውድመት ሲደርስ መሪዎቻችን ወደ ቀልባቸው ተመልሰው ሕዝቡ ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ እልህ ተጋብተው እንደዚያ ግትር መሆናቸውን ሳስብ በግሌ ለፖለቲካው ሩቅ ብሆንም በታሪክም ሆነ በባለጉዳዩ ሕዝብ ዘንድ በፍጹም ይቅር ሊባል የማይችል ስህተት እንደሆነ ይሰማኛል።

ለማንኛውም "መቃብር የተመኙለት ኢህአዴግ" ውሎ ሳያድር የተቀጣጠለው የሕዝብ ቁጣ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ራሳቸው ሥልጣን እንዲለቁ ምክንያት ሆኗል። የኢህአዴግም እስትንፋስ ጨልሞ ግባ መሬቱ ሊፈጸም ግድ ብሏል። ከለውጡ በኋላም አቶ ካሣ በአምባሳደርነት ከተሾሙበት ሀገር ሳይመለሱ ጥገኝነት ጠይቀው በባዕድ ምድር ለመቅረት ወስነዋል። ይህንን የወቅቱን ገጠመኞችንን በተመለከተ ያለ ምንም ፍርሃት "ማን ከማን ይታረቃል!?" በሚል ርዕስ የጻፍኩት አርቲክሌ በመንግሥታዊው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ጥር 6 ቀን 2012 ዓ.ም ታትሞ ለንባብ በቅቷል።

እነዚያ 120 የሰላም መልእክተኛ ጉባዔተኞች በጋራ የተስማሙባቸው የወቅቱ ችግሮች ምን ያህል ተቀርፈው ዛሬ ላይ መፍትሔ እንደተገኘ አንባቢው የራሱን አስተያየት ሊሰጥ ይችላል። በግል መረዳቴ ግን ያ የትናንቱ ብሶትና "ለመፍትሔ የጮኸንላቸው" ሀገራዊ መከራዎቻችን ዛሬም ድረስ ተጠናክረው ቀጥለው ካልሆነ በስተቀር ዕንቅቅልሻችን ተፈትቶና ሕዝቡ መፍትሔ አግኝቶ እፎይ ስለማለቱ እርግጠኛ አይደለሁም። እንዲያውም አንዳንዱ ባይከፋ! "ትሻልን ሰድጄ፤ ትብስን አገባሁ" በማለት ብሂሉን ያወረሰን አባወራ ምን ያህል ስሜቱ ቢጎዳ ኖሯል። ይብላኝልሽ ሀገሬ!

## ከበስተ ጀርባ የተላከብኝ ሰላዩ "ወዳጄ"

ያንን መዘዘኛ ስብሰባ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቢ ግቢ ውስጥ ባደረግንበት ሰሞን አራት ኪሎ አርበኞች ሕንጻ ላይ ከሚገኘው ቢሮዬ ወጥቼ በፓርላማው ዋና በር ፊት ለፊት ገባ ብሎ ወደሚገኝ አንድ ካፊቴሪያ ቡና ለመጠጣት ጎራ አልኩኝ። ወደ ካፊቴሪያው እንደገባሁ በአካዳሚክስ እውቀቱና በባህርይው መልካምነት የማከብረውና ከዓመታት በፊት ለፖለቲካ ሥርዓቱ ቅርበት ያለው ታጋይ መሆኑን በአንደበቱ ያጫወተኝን አንድ ወዳጄን አገኘሁት። ሞቅ ያለ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ "ሰሞኑን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቢዝነስና የኢኮኖሚክስ ፋክልቲ መሰብሰቢያ አዳራሽ

ውስጥ አንድ የምክክር ጉባዔ አዘጋጅተን ነበር። ብትገኝ እንዴት ደስ ባለኝ ነበር። ትዝ ቢለኝ ኖሮ እጋብዝህ ነበር።" ብዬ ንግግሬን ሳልጨርስ ይህ ወዳጄ "ጌታቸው ስብሰባው ውስጥ ነበርኩ እኮ!" በማለት መለሰልኝ። "በፍጹም በታዳሚዎች ሊስት ውስጥ ስምህን አላገኙሁትም። ማን ጋብዞህ መጣህ?" በማለት ግራ እየተጋባሁ ጠየቅሁት። "ጌታቸው ሙት ተገኝቻለሁ። እንደውም የተቀመጥኩት ከአንተ ጎን ነበር" በማለት አስረግጦ ሊያሳምነኝ ሞከረ።

ፕሮግራሙን ማስተባበሩና መምራቱ ናላዬን አዞሮት ስለነበር "ምናልባት ልብ ብዬ ያላየሁህ እየተዋከብኩ ስለነበረ ይሆናል። ከነበርክ ሁኔታውን እንዴት ገመገምከው? እያንዳንዱ ተሳታፊ በቃላት ሳይሆን የፍም አሎሎ ከአፉ እያስወነጨፈ ይሰጥ የነበረውን አስተያየት እንዴት ተረዳኸው። ለምን መንግሥት በዚህ ጉዳይ ቸል እንደሚል አይገባኝም። የሕዝብ ብሶት በጊዜው መልስ ካላገኘ ውሎ አድሮ..." ብዬ ልክ እንደተገኘ ታዳሚ በመቁጠር ገለጻዬን ሳራዝም በሳቁ አቋረጠኝ፡-

"ጌታቸው መገኘቱን አልተገኘሁም። ለማንኛውም ፕሮግራማችሁን በቅርበት እንዲከታተሉ በቂ የደህንነት ባለሙያዎችን አሰማርተን ስለነበር እየተቆጣጠርናችሁ ነበር። ይህንን ኃላፊነት የወሰድኩት እኔ ስለነበርኩ ‹ጉባዔውን እየመራ ያለው ጌታቸው ነው› ብለው ሪፖርት ሲያደርጉልኝ እንዲመለሱ አዝዣቸው የደህንነት ባለሙያዎቹ ተመልሰዋል። መቼም ጌታቸው ሀገሬ ሀገሬ እያለ ለሚጮህላት ሀገሩ ክፉ ያስባል ወይንም ያሳስባል ብዬ ስለማላምን የደህንነት ሠራተኞቹ እንዲመለሱ ያዘዝሁት በአቋምህ ስለማልጠራጠር ነው።" በድንጋጤ ክው ብዬ ቀረሁ።

"ለመሆኑ ከሙያህ ጎን ለጎን የደህንነት ሠራተኛ ነበርክ?" ብዬ ለጠየቅሁት ጥያቄ የሰጠኝ መልስ እጅግ አስገርሞኛል። ለማንኛውም የማውቀውን ያህል ለሥራ ትጉህ የሆነውና በአካዳሚክስ እውቀቱም በሳል የሆነው ይህ ወዳጄ የነገረኝ ነገር ዛሬም ድረስ እንደከነከነኝ አለ። ክትትሉ በሌላ ሰው ኃላፊነት ሥር ወድቆ ቢሆን ኖሮ ከዚያ ስብሰባ በኋላ ምን ሊፈጠር ይችል እንደነበር ለመገመት ያዳግታል። የእግዚአብሔር ጥበቃ አልተለየንም ነበር ማለቱ ይበጃል።

ከዚሁ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሌላም ጉዳይ ተፈጽሞ እንደነበር የተረዳሁት አብሮን ያገለግል ከነበረ አንድ ወንድም ነው። ከስብሰባው በፊትም ሆነ በኋላ የምክክር መድረካችን የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች በሙሉ እግር በእግር እየተከታተሉ ለመንግሥት የሚያደርሱ አንድ ሁለት ግለሰቦች ለካንስ በመካከላችን ነበሩ። የዚያን ዕለት የደረስንበትን የስብሰባችንን ማጠቃለያ ሪፖርት ለመደባቸው ከፍል ያደረሱት በዚያው ምሽት እነዚያው "የእኛ እንላቸው" የነበሩ ሰዎች እንደነበሩም ምሥጢሩን የነገረኝ ዘግይቶ መድረካችንን የተቀላቀለ አንድ የማምነው ወንድም ነበር። ለካስ ስንራመድ የኖርነው በጭቃ ውስጥ እሾህ ተከበን ኖሯል!?

"የፈሩት ይደርሳል፤ የጠሉት ይወርሳል" እንዲሉ መንግሥትና ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ የማታ ማታ ምን ደረጃ ላይ እንደደረሱና መጨረሻው ምን እንደሆነ የትናንት ታሪክ ስለሆነ ብዙ ማለት የሚያስፈልግ አይመስለኝም። የምክክር መድረካችንም ያንን ሁሉ ጥረት ቢያድርግም "እንደ ቁራ" ከመጮኽ በስተቀር ሰሚ ጆሮ በማጣቱ አባላቱ ተስፋ ቆርጠው እየሸሹ የማታ ማታ የመድረካችንም ህልውና ምዕራፍ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊዘጋ ግድ ሆነ። የማይበርድ የሀገር ፍቅር ባላቸው ነፃና ገለልተኛ ምሁራን ተቋቁሞ ለ12 ዓመታት ያህል እጅግ በርካታ ጥናቶችን በማድረግና የውይይት መድረኮችን በማመቻቸት የተጋው መድረካችን "እንደ መጥምቁ ዮሐንስ" በምድረ በዳ ተግቶ ቢጮኽም ሰሚ በመጥፋቱ እነሆ ታሪኩ በነበር ሊዘከር ግድ ስላለ ለታሪክ መዘክርነት ዘግቤዋለሁ።

የዛሬው ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን የተቋቋመበትን አካሄድና አንዳንድ በአዲሱ መንግሥት የተወሰዱ ፖለቲካዊ ውሳኔዎችን ለመንግሥት ካቀረብናቸው ሰነዶች ጋር ሳስተያያቸው የመድረካችን አሻራ ደመቅ ብሎ ይታየኛል። ዜጎች በሀገራቸው ጉዳይ የሚያነሷቸውን ዘርፈ ብዙ ጥያቄዎችን በተመለከተ መንግሥት ልብ ተቀልብ ሆኖ እየተከታተለ ተገቢውን መልስ መስጠት ካልቻለ በስተቀር ውጤቱ ከታሪኮቻችን ከተማርናቸው እውነታዎች የሚለይ ሊሆን እንደማይችል ሳስብ ስሜቴ በፍርሃት ሲቀዘቅዝ ይታወቀኛል።

ሕዝብ መንግሥትን የሚጠይቃቸው ጥያቄዎች በሙሉ በአንድ ጀንበር ምላሽ ይሰጣቸው ማለት አይደለም። ከቻለ ወዲያው ቅሬታው እንዲፈታ መልስ ለመስጠት ቢሞከር መልካም ነው። ካልሆነለትም "ጥያቄችሁንና ፍላጎታችሁን ለመመለስ ጊዜ ስጡኝና በመፍትሔዎቹ ላይ ላስብበት" ቢል ጨዋነት ነው። ጥያቄዎቹ በፍጹም ከሀገራዊው እውነታና ከጊዜ አንፃር ሊጠየቁ የማይገባቸው ከሆነም ምክንያቱን በዝርዝር በመግለጽ "ለጊዜው ልንፈጽም የምንችልበት ደረጃ ላይ አይደለንም" በማለት ቁርጥ ያለ መልስ ቢሰጥ ሕዝቡ ቁርጡን አውቆ ሊረጋጋ የሚችል ይመስለኛል። ከዚህ እውነታ በተለየ መልኩ ግን ሕዝብ በለሆሳስም ሆነ በእዮታ እየተንገበገበ "በሕግ አምላክ! በቅዱሳት መጻሕፍት አምላክ! ወይንም በጉልበት አምላክ!" እያለ ለሚጮኽባቸው ወቅት ወለድ ሀገራዊ ብሶቶች መንግሥት ዝምታ መርጦ "ምንም የሚፈጠር ነገር አይኖርም" በማለት በሥልጣን ጡንቻ መመካት መጨረሻው ምን ሊሆን እንደሚችል ቀደምቱና የቅርቦቹ ታሪኮቻችን ህያው ምስክሮች ናቸው።

"ያለፈው ጥረታችንን ሳስታምመው ትዝ ሲለኝ፣
ከሞከርነው ነገር ይልቅ ያልሞከርነው ነው የሚቆጨኝ።"

በማለት ምናባዊው ደራሲ ጸጋዬ ገብረ መድኅን ይህንን በእውነታ የታመቀ ስንኝ ትቶልን አልፏል። እኛስ ከሞከርነው ይልቅ ያልሞከርነውን ማየት ብንችል መልካም አይሆንም? መድኃኒት ለመፈለግ ዳተኛ የሆንባቸው ብሔራዊ በሽታዎቻችን አንድም የልብ ጥበት፣ አንድም የመተማመን ሽሽት፣ አንድም "የምን ይመጣል" ትምክህት፣ አንድም የመረረ ጥላቻ ህመም፣ አንድም የዘር ትምክህትና ደዌ፣ አንድም "የበላይነት ክፉ ነቀርሳ" አንድም ሕዝብ የጠላውን ፖለቲካዊና ርዕዮታዊ ጉድፎች የሙጥኝ ማለቱን እየጠቃቀሱ መዘርዘር ይቻላል። እነዚህ ህመሞች ሲወርዱ ሲወራረዱ የመጡ ብሔራዊ ካንሰሮቻችን ነበሩ፤ ናቸውም።

ይሄው ብሔራዊ አበሳችን ምናልባት መፍትሔ ያገኝ እንደሆን በመመኘትም ፖለቲከኞቻች ቀልብ እንዲገዙ ጠንከር በሚል የብእሬ ድምጸት ከማሳሰብ አልቦዘንኩም። በዚህ ሃሳብ ላይ በመንግሥታዊው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ከጻፍኳቸው እጅግ በርካታ አርቲክሎች መካከል፡- "የዘመነ ብልጽግና ተስፋና ስጋታችን"፣ "ኅበዝ እንዴት ነው ጉዳዩ?"፣ "ቢጋራ ጉዳይ ጠላትነት፤ በግል ጉዳይ ጀግንነት"፣ "ምድረ ኖድ የቃየን ማረፊያ"፣ "የሀገሬ ብሔሯ ምንድን ነው?፣ "በሀገሬ ሉዓላዊነት እስማማለሁ፤ ሕዝባችንስ ሉዓላዊ ነው"፣ "ዘመንኛው የሀገራችን ‹ዘመነ መሣፍንት›"፣ "ዲሞክራሲ የፖለቲከኞች ልቦለድ"፣ "ይዋጣልን ይሉት ዓይነት የፍልሚያ ሽማ መጣጣል"፣ "በፓርቲ ያልተደራጀው ሕዝብ በንቃት ከፖለቲከኞቻችን ቢልቅ እንጂ አያንስም"፣ "ሀገር የማን መልክና ምሳሌ ነች" ወዘተ. በሚሉ አርእስት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ያስነበብኳቸው መራር ጽሑፎች የቁዘማዬ ውጤቶች ናቸው።




*Prolific author, diplomat and scholar Getachew Bellete shares his gripping memoir of hiding as rural shepherd. Sustained by strong faith, he detailed his struggle for survival and resistance under the cruel Ethiopian communist regime.*

**The Pen and the Shield - Amharic Edition**
By Getachew Bellete

**Order the book from the publisher Booklocker.com**
https://booklocker.com/books/14888.html?s=pdf
**or from your favorite neighborhood or online bookstore.**